ምእራፍ ፡ ፷፰

ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ መስቀል ፡

ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ከታሰረችበት ፡ ባስረኛው ፡ ቀን ፡ እስክትፈታ ፡ ድረስ ፡ አባትዋም ፡ እግራቸው ፡ በግር ፡ ብረት ፡ ውስጥ ፡ አይግባ ፡ እንጅ ፡ እንደሰዋ ፡ አሰረኛ ፡ ሆነው ፡ ሰነበቱ ።

የጅዋ ፡ መታሰር ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ ልብስ ፡ በመልበስም ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ ስለፈጠረ ፡ ወዳያውም ፡ እሳቸው ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ ካጠገብዋ ፡ የማይለዩ ፡ በመሆናቸው ፡ የማያስፈልግ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ በታሰረች ፡ ግማስት ፡ እጅዋን ፡ እንድትፈታ ፡ ተደረገ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለት ፡ ወይም ፡ ሹል ነት ፡ ያለው ፡ ብረትም ፡ ሆነ ፡ እንጨት ፡ ባጠገብዋ ፡ እንዳይደርስ ፡ የምትበላውንም ፡ ሆነ ፡ የምትጠጣውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያ ፡ በሳቸው ፡ ፊት ፡ አቅራቢዎቹ ፡ ሳይቀምሱት ፡ ለሰዋ ፡ እንዳይቀርብላት ፡ አጥብቀው ፡ ይጠነቀቁ ፡ ነበር ።

ፈታውራሪ ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ልጃቸውን ፡ ሲጠብቁ ፡ ፊትዋ ፡ ህይወት ፡ እንደሌለው ፡ ጥሩ ፡ ምስል ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ አይኖችዋ ፡ ቡዝዝ ፡ ብለው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተተክለው ፡ ይቆዩና ፡ ድንገት ፡ እንባዋ ፡ በጉንጭዋ ፡ ያወጣውን ፡ መንገድ ፡ ተከትሎ ፡ ሲሄድ ፡ የማያቋርጥ ፡ ሳግ ፡ ሲተናነቃት ፡ ያዩና ፡-

“ወይ ፡ እኔ ፡ መሸሻ ! ይህ ፡ አጥንጅ ፡ ይህ ፡ አስግተኛ ፡ ተግሪ ፡ በልጄ ፡ ተጫወተባት ! ምነው ፡ ጌታየ ! ላንድ ፡ አፍታ ፡ በጀ ፡ ጥለሽው ፡ በልጄ ፡ እንደተጫወተ ፡ ጀርባውን ፡ የዝንብ ፡ መጫወቻ ፡ ባደርገው ! ሌላ ፡ ምንም ፡ አልሰም ንህም ! ይህን ፡ ብቻ ፡ ጌታየ ! ይህን ፡ ብቻ ፡ አድርግልኝ !” ይላሉ ፡ በብርቱ ፡ ስሜት ፡ አይኖቻቸውን ፡ እግዚአብሄር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንስተው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረሰኞች ፡ የግንኩሳን ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ የደብረ ፡ ወርቅንና ፡ የሲኖዳን ፡ መንገድ ፡ እዩተከተሉ ፡ እግረኞች ፡ ዲግ ፡ ውስጥ ፡ የበዛብህ ፡

ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ የሚባሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ በዩም ክናያቱ ፡ እዩገቡ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በዛብህን ፡ ፈልገው ፡ ስላጡት ፡ እንያማያገኝ ፡ ተስፋ ፡ ተቆርጠ ፡ ፈታውራሪ ፡ መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቅ ፡ ሌላ ፡ ስው ፡ በምስጢር ፡ ተፈልጎ ፡ ቢገኝ ፡ የጠዬቀውን ፡ ዋጋ ፡ አሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ያስፈልጉ ፡ ጀመር ።

በዛብህ ፡ በዘዙሉ ፡ የፍቅርና ፡ የፍራት ፡ አስረኛ ፡ ሆኖ ፡ እጉዳ ፡ ካሳ ፡ ቢጎ ፡ ተሸሽጎ ፡ ብሰብስ ፡ የደረሰው ፡ ከሰማው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጎልቶ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በርክቶ ፡ እዩታዬው ፡ ነጻ ፡ ሳሰች ፡ የነበረችውና ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሆነችው ፡ እዩተለዋ ወጠ ፡ እዩታዬው ፡ የሚበላው ፡ ባፉ ፡ እየተንከራተተ ፡ አይ ዋጥለት ፡ ቢተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ አያወስደው ፡ እያደር ፡ እንደ ፡ ቀረፈተት ፡ ዛፍ ፡ እዩጠወለገና ፡ እዩደረቀ ፡ ይታያ ፡ ነበር ።

“ያሰሩዋት ፡ እኔን ፡ አስማት ፡ አድርጎባታል ፡ ብለው ፡ ከሆነና ፡ እኔ ፡ ሄጀ ፡ ፈታሁ ፡ ካላልሁ ፡ የማያፈትዋት ፡ ከሆነ ፡ አሁን ፡ ብሄድና --- ነአኩቶበን ፡ ወይም --- ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ደግሚ ፡ ፈትቻታለሁ ፡ ብል ፡ ምናሰ ? መቸም ፡ ፪ም ደግመውን ፡ እያሰግዘ ፡ ድግም ፡ አይሉኝ !” አለ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ጋር ፡ ይህኑ ፡ ነገር ፡ እንስተው ፡ ሲወያዩ ።

“ነገሩ ፡ በዚህ ፡ ብቻማ ፡ የሚያልቅ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ያስቸግር ፡ ኖሮዋል ?”

“ታዲያ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ይኖራል ?”

“ምነው ፡ ነግሬህ ፡ የሰም ? እገርፈዋለሁ ፡ ብለውኮ ፡ ነው ፡ የሚፈክሩ ! ደግሞ ፡ ካገኙህ ፡ እንደ ፡ ፈከሩት ፡ ማድረጋቸው ፡ አይቀርም ፡ ባስጌ ፡ ናቸው !”

“ታዲያ ፡ ይግረፉኝ ፡ እንጂ ፡ ምናሰ ! አሰዋ ፡ ታስራ ፡ ከምትሰቀይ ፡ ይግረፉኝ ! ነገ ፡ የሚድን ፡ ቁስል ፡ አይደል ?”

“አዎ ፡ የተገረፈ ፡ ጀርባ ፡ ቶሎ ፡ ይድን ፡ ይሆናል ፡ የተሰበረ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ እንጃ !”

“እንዴት ?”

“ስትገረፍ ፡ አይታ ፡ ወይም ፡ መገረፍህን ፡ ሰምታ ፡ ሰው ፡ የምትሆን ፡ ይመስልሀል ? ባትሞት ፡ ልብዋ ፡ እንደ ፡

ተሰበረ ፡ ይቀራል ። ለምን ፡ ሰደቡት ፡ ብላ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ያለቀሰች ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የምትሆነውን ፡ ያጣች ፡ መሬፍ ሀን ፡ ያጬች ፡ ወይም የሰማች እንደሆነ ፡ ሰው ፡ እንደማት ሆን ፡ አውቃለሁ ። ስለዚህ ፡ ከምትሞት ፡ ወይም ፡ ልብ ፡ የሚ ሰብር ፡ አዘን ፡ ከሚደርስባት ፡ ታሰራ ፡ ብትቆይ ፡ ይሻላል ። ወዲያውስ ፡ ስንት ፡ ቁን ፡ አለረው ፡ ያኖርዋት ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ይፈትዋታል !”

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲናገር ፡ በፅብህ ፡ እንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ እዩ ሰማ ፡ እንባው ፡ ፊቱን ፡ ሳያነካ ፡ እመራት ፡ ላይ ፡ ይንጠባጠብ ፡ ነበር ።

እውነትም ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንዳለው ፡ መፍትሄ ፡ ጸርጎ ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚያው ፡ ዲግ ፡ ተገ ኝተው ፡ መፍትሄውን ፡ ስላደረጉላት ፡ ሰብለ ፡ በታሰረች ፡ ባስረ ኛው ፡ ቀን ፡ ተፈታች ።

“ ጌቶች ! አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለብኝ ፡ ባንጋግርዎ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡ ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ እልፍኛቸው ፡እሰ ብለ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠው ፡ ዳዊት ፡ በሚደግሙበት ፡ በች ኮላ ፡ ገብተው ።

“ ወዬው ፡ ጉድ ! ምን ፡ እንደማደርግ ፡ አያዩም ? ዳዊ ቴን ፡ አቁዋርጪ ፡ ነው ፡ እሰዎን ፡ የማነጋግር ?”

“ ግዴለም ፡ ያቁዋርጡት ፡ ዋኖ ፡ ነገር ፡ ነው ! ”

ከዚያ ፡ ፊታውራሪ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እሳቸውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ካልያዙ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እንደማይደ ፍሩ ፡ ስለሚያውቁ ፡ ያባ ፡ ሞገሴን ፡ ቃል ፡ ለማክበር ፡ ሳይ ሆን ፡ ወሬያቸውን ፡ ለመስማት ፡ በመቸኮል ፡ ዳዊታቸውን ፡ አጥፈው ፡ በሩን ፡ ወጣ ፡ አሉኖ ፡ ሰብለን ፡ ለማየት ፡ በሚችሉ በት ፡ ቦታ ፡ ሄደው ፡ ቆሙ ።

“ የምስራች ! ” አሉ ፡ አባ ፡ ሞገሴ ፡ ሰብለ ፡ እንዳት ሰማ ፡ ድምጻቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ።

“ ምስር ፡ ይብሉ ! ምንድነው ? ”

“መፍትሄ ፡ ጸርጎ ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰው ፡ እዚሁ ፡ እኛ ፡ ዘንድ ፡ ተገኙ ። ”

“ የት ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዓይታቸው ፡ ሁሉ ፡ በቅጽ በት ፡ ተላውሶ ። ከደስታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ፈገግ ፡ እን ዳሉ ፡ ከንፈሮቻቸውኖ ፡ ጉንጮቻቸው ፡ ሲንቀጠቀጡ ፡ አይናቻ ቸው ፡ እንባ ፡ ሲሞሉ ፡ ይታዩ ፡ ነበር ።

“ እዚሁ ፡ ዲግ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ የሚባሉ ፡ መነኩሴ ፡ ናቸው ። ”

“ መቸ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ? ”

“እ —ከመጠሰ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ፤ ብቻ ፡ ከመቃብር ፡ ቤታቸው ፡ አይወጡም ፡ እንዳንድ ፡ ምክር ፡ ሊጠይቁዋቸው ፡ ከሚሄዱ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ በቀር ፡ ከብዙ ፡ ሰውም ፡ አይገናኙ ። ”

“ ታዲያ ፡ እሰዎ ፡ እንዴት ፡ አወቁዋቸው ? ደግሞስ ----እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰው ፡ ከሆኑ ፡ ይህን ፡ ነገር ---ደህና ፡ አድር ነው ፡ የሚያውቁ ፡ ይመስልዎታል ? ” አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መጠራጠር ፡ አሉኖ ።

“ እኔማ ፡ በዱጊዜው ፡ እዩሄድሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ ምክር ፡ ስለምጠይቃቸው ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ አውቃቸዋለሁ ። ይህ ፡ ነገር ፡ ከደረሰብን ፡ ወዲህ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ የማይነገር ፡ ስለ ሆነ ፡ እስቲ ፡ እግዚአብሄር ፡ ከኛ ፡ ለሳቸው ፡ ቅርብ ፡ ነውና ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ የሚገልጸላቸውን ፡ መንገድ ፡ ያሳዩን ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ሄጀ ፡ በምስጢር ፡ ባዋያቸው ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ላደርገው ፡ እችላለሁ ፡ ” አሉኝ ።

“ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ ዘርገረው ፡ ነግረዋቸው ፡ አውቃለሁ ፡ አሉ ? ”

“ አዎ ፡ ለማንም ፡ የሚነገር ፡ አለመሆኑን ፡ ጭምር ፡ አደራ ፡ ብዬ ፡ ነግሬያቸው ፡ ለሁሉም ፡ ግዴለም ፡ ብለው ኛል ። ”

“እንግዲህ ፡ ግታ ፡ ያምጡዋቸውና ፡ ለብኝ ፡ ላነጋግራ ቸው ። ”

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ ልደታቸው ፡ በወሊጋ ፡ ውስጥ ፡

ቱድሩ ፡ በሚባል ፡ ክፍል ፡ ነው ። በልጅነታቸው ፡ በዘር ፡ መዝሪያ ፡ አካላቸው ፡ አደጋ ፡ ደርሶባቸው ፡ ወዲያው ፡ ቀስለ ፡ እንደ ፡ ዳን ፡ ከዘመዶቻቸው ፡ ኩብልለው ፡ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ተሻ ግረው ፡ ካንዱ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ እዩተዘዋወሩ ፡ ንባብና ፡ ዜማ ፡ ከዚያም ፡ ትንሽ ፡ ቅኔ ፡ ከተማሩ ፡ በሁዋላ ፡ መንኩሰው ፡ ከጎጃም ፡ አድባራትና ፡ ገዳማት ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ አመት ፡ ያልተቀመጡበት ፡ አይገኝም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዲግ ፡ ከተቀመጡ ፡ አንድ ፡ አመት ፡ አልፎዋቸዋል ። በደረሰባቸው ፡ አደጋ ፡ ምክናያትም ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ ከፍጥ ረታቸው ፡ ነሰው ፡ ጋዝ ፡ ከመፈጠር ፡ ብቸኛነትን ፡ ከመና ገር ፡ መሰማትን ፡ የሚመርጡ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። ብዙ ፡ ሰምተው ፡ ትንሽ ፡ የተናገሩ ፡ እንደሆነም ፡ ያኑ ፡ ትንሹን ፡ ሳያዛቡት ፡ ወዝፈው ፡ ስለሚተውት ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ የሚተረጎም ፡ ይሆንና ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ " አባ ፡ ተክለሃይማኖትማ ፡ ብለው ፡ ነበር ፡ " የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ባለ መጥፋቱ ፡ አዋቂ ፡ ባህታዊ ፡ ይባላሉ ። " አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖትን ፡ ለማናገር ፡ ቀጥሎም ፡ የተናገሩትን ፡ ለማስተዋል ፡ ከተቻለ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ታላቸው ፡ አመራት ፡ ጠብ ፡ አይ ልም ። " ይባላል ።

ስለዚህ ፡ እንደሳቸው ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ በጸሎት ፡ ለተጠመዱ ፡ ምእመናን ፡ ከቤተክርስቲያኑ ፡ ከሚ ላከላቸው ፡ መሀራ ፡ ሌላ ፡ በመልክም ፡ በወሬም ፡ የሚያው ቁዋቸው ፡ ሰዎች ፡ " አያረሱን ፡ " እያሉ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ልብሰም ፡ ገንዘብም ፡ እዩላኩላቸው ፡ ይህና ፡ ይቀመጣሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አዘውትረው ፡ የሚለብሱት ፡ ደበሎ ፡ ስለሆነ ፡ ሰው ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ጋቢም ፡ ሆነ ፡ ኩታ ፡ መልሰው ፡ ልብስ ፡ ለሌላ ቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሰጡታል ። እንዲሁም ፡ ገንዘብና ፡ መጠጥ ፡ ሲ ሰጡ ፡ አይታዩም ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ከሚልክላቸው ፡ ምግብ ፡ የሚበ ልጠውን ፡ መሽት ፡ ሲል ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ ደጀሰላምና ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ለወደቁ ፡ ድሆችና ፡ በሽተኞች ፡ እዩዞሩ ፡ ይመ ጸውታሉ ። ታዲያ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያዬ ፡ ስለሚያወራ ፡ ተመጽው ተው ፡ መመጽወታቸውም ፡ የሚመጸውቷቸበት ፡ ሁኔታም ፡ ለት

ልቅ ፡ ጸድቅነታቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክር ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርላቸው፡ ነበር ።

ፈታውራሪ ፡ አባ ፡ ምነሴንና ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ በቀጠሩበት ፡ ማታ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ምሽታቸውን ፡ ከሰ ብለ ፡ ጋር ፡ አሰቀምጠው ፡ " ስእል ፡ ቤት ፡ " በሚሉዋት ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ብቻቸውን ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጠብቁ ፡ የንስሀ ፡ አባታቸው ፡ እንግዳውን ፡ ይዘው ፡ ደረሱ ።

አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መልከ ፡ ቁና ፡ እንደሳቸው ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዘለግ ፡ ብለው ፡ ከትክሻቸው ፡ ትንሽ ፡ ሰግደድ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ልብ ሳቸውም ፤ ቆባቸውም ፡ ደበሎ ፡ ነው ።

ከርዝመታቸውና ፡ ከቅጥነታቸው ፡ የተነሳ ፡ የለበሱት ፡ ደበሎ ፡ በረዥም ፡ መስቀያ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተንጠለጠለ ፡ ሁሉ ፡ ከጉልበታቸው ፡ በታች ፡ ረዥም ፡ ቅልጥማቸውን ፡ ራቁት ፡ አድርጎ ፡ ባሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ የተጠቀለለ ፡ ነገር ፡ በሁለት ፡ እጆ ቻቸው ፡ ቀደም ፡ አድርገው ፡ ይዘው ፡ ፈታውራሪን ፡ ምሀረት ፡ እንደሚለምኑ ፡ ሁሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ቀልሰው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍሱ ፡ አፈታቸው ፡ ቆሙ ። ሲገቡ ፡ ሰላምታ ፡ እንኩዋ ፡ ባለመስጠታቸው ፡ ፈታ ውራሪ ፡ ገርሞዋቸው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ አያናቸውን ፡ ፍጥጥ ፡ እድርገው ፡ ይመለከቱዋቸው ፡ ጀመር ።

"ጌቶች ! አባቴ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ።" አሉ ፡ አባ ፡ ምነሴ ፡ የተፈጠረውን ፡ ሁኔታ ፡ ሲያዩ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሸበር ፡ አሉና ።

" እህ ---- እሳቸው ፡ ናቸው ? እንደምን ፡ ነዎ ፡ አባቴ ! " አሉ ፡ ፈታውራሪ ። አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አንገታቸውን ፡ ከደፉበት ፡ አውንም ፡ ትንሽ ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ፡ ሰላምታውን ፡ ለመመለስ ።

" ይምጡ ፡ እዚህ ፡ ይቀመጡ ! " አሉና ፡ ፈታውራሪ ፡ መቀመጫ ፡ ላባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እያሳዩ ፡ አባ ፡ ምነሴን ፡ እውጭ ፡ ቆመው ፡ ሰው ፡ ሲመጣ ፡ እንዲከለክሉ ፡ አዘዙዋ

ቸው ።
“ የደረሰብ
አሉ ፡ ፊታውራሪ
ደፍተው ፡ እንደ ፡ ተ
“ አ -- አዎ ! ”
“ ታዲያ ፡ ይ ንልዎ
“ ለግዚአብሄር ----- የ
“ ለግዚአብሄርማ ፡ ም
መፍትሄ ፡ ጸርና ፡ መፍት
ያስመጣሁዎ ! ይህን ፡ የመ
ርገዋል ፡ ወይ ፡ ግለቴ ፡
“ እኔስ --- እ ን ፡
“ ድጋም ፡ ነው ? ወያ
አባ ፡ ተከለ ፡ ሀይማ
መልስ ፡ በመስጠት ፡
የያዙትን ፡ ነገር ፡ ገልጠ
“ እስ --- መስ
ርጋሉ ? ”
“በሰው ፡ አጅ ፡ የተሰ
“ታዲያስ ? ”
“ አስራ ፡ አምስት ፡
ባንድ ፡ እግሬ ፡ ቆ ፡
ቃቤ ፡ ስራይ ፡ በጸላ ፡ ስና
ነው ! ”
“ነማን ፡ ነው ፡ የተ
“ ጸሎቱ ፡ ላረገለት ፡
“ ከእግዚአብሄር ፡ የ
አባ ፡ ተከለ ፡ ሀ
ዝም ፡ ብለው ፡ ቆዩና
የሚያስቸግር ፡ ነገር
ማታ ----እዚሁ ፡ ቦ
ለመሄድ ፡ ተነሱ

ቀላቸውን ፡ ከተጠቀለለበት ፡ አሮኔ ፡ ሠሬቅ ፡ ይፈቱ ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ የብረት ፡ መስቀላቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይዘው ፡ ትንሽ ፡ ወደ ፡ ሳብለ ፡ ቀረብ ፡ ብለው ፡ እግሮቻቸውን ፡ ገጥመው ፡ ቆመው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ይደግሙ ፡ ጀመር ። አፋቸው ፡ ሲነቃነቅ ፡ ከመታየት ፡ በቀር ፡ ድምጻቸው ፡ አይሰማም ። ይደግሙ ፡ ይደግሙና ፡ እፍኙ ፡ እፍኙ ፡ እያሉ ፡ አዩ ሩን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ በመስ ቀሉ ፡ ይቀዝፉታል ። እንዲህ ፡ ላይና ፡ ታች ፡ እያዩ ፡ ሲደግሙ ፡ እፍኙ ፡ እፍኙ ፡ እያሉ ፡ አዩሩን ፡ በመስቀል ፡ ሲቀዝፉ ፡ ደግሞ ፡ ሲደግሙ ፡ ደግሞ ፡ አዩሩን ፡ ሲቀዝፉ ፡ ብዙ ፡ ቆይተው ፡ በመጨረሻ ፡ ወደ ፡ ሰብለ ፡ ቀረብ ፡ አሉና ፡ ጎንበስ ፡ ብለው ፡ “መስቀሉን ፡ ሳሚ !” አሉ ። ሰብለ ፡ መስቀሉን ፡ ሳመች ።

“ ተሳለሚው ! ”

ሰብለ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ። ከዚያ ፡ መስቀሉን ፡ ገልብጠው ፡ ያዙና ፡- “በይ ፡ አፍሽን ፡ እመስቀሉ ፡ ላይ ፡ ግንባ ርሽን ፡ እመያዣው ፡ ላይ ፡ አሳርፈሽ ፡ ትንሽ ፡ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ቆይና ፡ በሁዋላ ፡ ለምጠይቅሽ ፡ ትመልሽልኛለሽ ፡”

አሁንም ፡ ሰብለ ፡ እንደ ፡ ታዘዘችው ፡ አደረገች ።

“አይንሽን ፡ ጨፍኚው !”

“ እሺ ፡ ”

“ ምን ፡ ይታይሻል ? ”

“ምንም ፡ አይታዩኝ ”

“ ምን ፡ ይሰማሻል ?

“ ምንም ፡ አይሰማኝ ! ”

“ እሰቲ ፡ አስቢና ፡ መጀመሪያ ፡ ባሳብሽ ፡ ውስጥ ፡ የሚመጣውን ፡ ንገሪኝ ! ”

“ እሺ ። ”

“ አሁን ፡ ባሳብሽ ፡ ምን ፡ መጣ ? ”

“መስቀል ፡ ሀይልን ፡ መስቀል ፡ ቤዛን ፣ መስቀል ፡ ጽንን ፣ መስቀል ፡ መድሀኒተ ፡ ነፍስን ፡ የሚለው ፡ ንባብ ፡ ታሰበኝ ! ”

“ መልካም ! ሌላ ---- ምንም ፡ አልታሰበሽ ? ”

“የለም ።”

“ይህን ፡ ሁሉ - - - - ችግር ፡ ያመጣብሽ ፡ ሰው ፡ አልታ ሰበሽም ?”

ሰብለ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ቆዩችና ፡ የ --- የለ --- የለም ፣” ስትል ።

አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መስቀሉን ፡ ይዘውላት ፡ እንዳጎነበሱ ፡ በጃቸው ፡ ለበላ ፡ ያለ ፡ ውሀ ፡ የፈሰሰባቸው ፡ መስሎ ፡ ተሰማ ቸውና ፡ እንደ ፡ መደንገጥ ፡ ብለው ፡ -- “እንግዴህ ፡ በቃ ፣ ቀና ፡ በይ ! ”አሉ ።

ከዚያ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ መስቀሉም ፡ እጃቸውም ፡ የታጠበበ ትን ፡ እንባ ፡ መስቀላቸውን ፡ በሚጠቀልሉበት ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅ ፡ ጠራርገው ፡ አድርቀው ፡ ሲያጨበጭቡ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቶሎ ፡ መጡ ።

“ለብቻዎ ፡ ላነጋገርዎና ፡ ልሂድ ! ”አሉ ፡ መነኩሴው ።

ፊታውራሪ ፡ ሰብለን ፡ ደግፈው ፡ አሰነስተው ፡ ወደል ፍኛቸው ፡ ወስደው ፡ ከናትዋ ፡ ጋር ፡ ካሰቀመጥዋት ፡ በሁዋላ ፡ ተመልሰው ፡ መጥተው ፡ እመደባቸው ፡ ላይ ፡ ሲቀመጡ ፡ “ይበሉ ፡ እንግዴህ ፡ ሁሉንም ፡ ይንገሩኝ ፡ አባቴ ! እደራዎ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይሰውሩኝ ! ”አሉ ፡ በዛብህ ፡ ልጃቸውን ፡ ያቆራኙት ፡ ክፉ ፡ መንፈስና ፡ ያደረገባት ፡ አስማት ፡ ምን ፡ አይነት ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ እጅግ ፡ ቸኩለው ።

“ከንግዲህ ፡ ----ምንም ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ----የለም ! ” አሉ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡ በጣም ፡ በለሰለሰ ፡ ድምጽ ፡ እንባታቸ ውን ፡ ደፍተው ።

“ ምን ፡ ኖሮዋል ፡ ለመሆኑ ? ጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ነው ? ”

“የለም ፡ ጸላኤ ፡ ሰናይ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ - - - አይደለም ! ”

“ታዲያስ ? ”

“ብርቱ ፡ አስማት ፡ ብርቱ ፡ ድጋም ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደና ፡ እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡ ከሱ ፡ በቀር ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያስጠላ ፡ ድጋም ፡ ነበር ፡- ተፈታ ፡ አሁን ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ---የለም ፡ ”

"እንዴትከ ---እዚህ ፡ አገር ፡ ያልተለመደ ፡ ከሆነ ፡--- እዚህ ፡ አገር ፡ ሊፈታ ፡ የማይቻል ፡- - - ከሆነ ፡ እንዴት ፡ ነው ?" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ በሻከረ ፡ ድምጽ ፡ ልቅሶ ፡ መጥቶባቸው ።

"ነየት ---እንደ ፡ ተማረው ፡ እንጂ ! ብቻ ፡ ለመፍታት ፡ ግን ፡---መቸም ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ባለመሆኑ ፡ የመስቀሉ ፡ ስልጣን ፡ ካጽናፍ ፡ እስካጽናፍ ፡ በመ ሆኑ ፡ የማይፈታው ፡ አስማት ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ተፈታ ።"

"እም ፡ እግዚአብሄር ፡ ጥሎ ፡ አይጥለኝም ፡ እግዚአብሄር ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እግዚአብሄር ፡ ስላልጣለኝ ፡ ነው፡ አስምን ፡ የጣለልኝ !" አሉ ፡ ፊታውራሪ ፡ አይኖቻቸው ፡ እንባ ፡ ሞልተው ፡ የእግዚአብሄርን ፡ ስም ፡ ባንሱ ፡ ቁጥር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ እያዩ ።

"እንግዲህ ፡---ልጅ፡ ፡ ተፈታ ! ብቻ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው !"

"እንዴት ?"

"ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የደረሰው ፡ ነገርና ፡---የሰውዬው ፡ ስም ----በፊትዋ ፡ እንዳያነሳ ፡ ከሞላ ፡ ፈዛዛው ፡---እዩተቀነሰ ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ----እንዲተረክላት ፡ ማድረግ ፡ መልካም --- ነው ! "

"እዩ ፡ አባቴ ፡ የሚዋ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ አሱም ፡ ትልቅ ፡ ለው ፡ እጅዋን ፡ ለምነኝ ፡ ለመስጠት ፡ አሰቢያለሁ ፡ ታዲያ --- ምን ፡ ይመስልዎታል ? "

"አሱማ ፡---ደንቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ! እስከዚያ ፡ ግን ,----- እንዲህ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። "

"እስከ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ?"

"የሶስት ፡---ያራት ፡ ወር ፡ እደሚ ፡"

"ያን ፡ ያክለስ ፡ መስናዶውም ፡ ይፈጃል ! ታዲያ ----- ለዚህ ፡ አጭር ፡ ጊዜ --- እስዎ ፡ ባጠገብዋ ፡ ሆነው ፡ ቢመክሩ ዋትና ፡ አሁን ፡ እንዳሉት ፡----የሚሰማማውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ታሪክ ፡ እዩመረጡ ፡ ቢተርኩላት ፡ ይመችዎታል ?"

"ምን ፡ ከፋኝ ፡ ነበር ! ነገር ፡ ግን - - - - ለብዙ ፡ ሰው ፡ ነፍስ፡ ባለአደራ ፡ ስለሆንሁ ፡ ጸሎት ፡ እንዳይታጎልብኝና ፡ ደግሞ - - - -

ከምእመናን ፡ እዩተመጸወትሁ ፡ የምመጸውታቸው ፡ ድውያን ፡ እንዳይቸገሩብኝ ፡ ነው ፡ እንጂ !" አሉ ፡ አባ ፡ ለመስማት ፡ በሚያ ስቸግር ፡ ዝቅተኛ ፡ ድምጽ ።

"ጸሎትዎን ፡ ሲጨርሱ ፡ የሚሰጡዋት ፡ ምክር ፡ ይዘቃል ! ለምጸዋቱ ፡ ግን ፡ ጭራሽ ፡ አያስቡ ፡ አህል ፡ ውሀም ፡ ይሁን ፡ ገንዘብ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ያክል ፡ እንሰጥዎታለን ! ልጂ ፡ ደህና ፡ ሆና ፡ ያባት ፡ ወግ ፡ ከደረሰኝ ፡ ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ገንዘብ ፡ ቆጥቤ ፡ የማደርገው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ እንኩዋን ፡ ዛሬ ፡ ድሮም ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣቢ ፡ አይደለሁም ።"

"እሱ፡ ፡ ጸሎት ፡ አድርጌ ፡---የእግዚአብሄርን ፡ ፈቃድ ፡ ልጠይቅና ፡---መልሱን ፡ ነገ ፡ አባቴ ፡ ሞጣ ፡ መጥተው ፡ ልንገራቸው ። "

"መልካም ! እንግዲህ ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ይሂዱ ! የድካምዎንም ፡ አሀን ፡ እሰጥዎታለሁ ! "አሉና ፡ ፊታውራሪ ፡ ገንዘብም ፡ መጠጥም ፡ ለመስጠት ፡ መነኮሴውን ፡ ይዘው ፡ ወደልፍኝ ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፡- - - "መጠጡ ፡ ነው ፡ እንጂ - - - ገንዘቡ ፡ ለኔ ፡ አይደለም ፡ አሁን ፡ ወስጂ ---ለተቸገሩ ፡ ደሆች ፡ የምመጸውተው ፡ ነው ፡ የምመጸውተውም ፡ ስለራሴ ፡----- አይደለም ፡ ስለመጸወትኝ ፡ ሰዎች ---ነው ! "አሉ ፡ አባ ፡ ተከሌ ።

" ነው ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ ነው ! እሰዎማ ፡ ምን ፡ ሀጢ አት ፡ ኖሮብዎ ፡ ይመጸውታሉ ! ስለኛ ፡ ስለሁላችን ፡ ነው ! "

በዘነጋው ፡ አባ ፡ ሞጣ ፡ መጥተው ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይ ማኖት ፡ ጸሎት ፡ አድርገው ፡ ፊታውራሪ ፡ የጠየቁትን ፡ ለመ ፈጸም ፡ የተፈቀደላቸው ፡ መሆኑን ፡ እስታወቁ ።

የሰብለን ፡ መፈታት ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ በዛብህም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ከታለረች ፡ ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንኩዋን ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ የሳቸ ውንም ፡ ያክስቱንም ፡ አያን ፡ ማየት ፡ በሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ሲያስባ ቸውም ፡ ሆዱ ፡ መታወክና ፡ ምራቁ ፡ ባፉ ፡ ውስጥ ፡ መምረር ፡ ይጀምራል ። በዛብህ ፡ መቸም ፡ እዩፈራ ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ ነው ፡ የሚውል ። ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡ ውጭውን ፡ የሚያየው ፡ ግቻ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ።

ሰብለ ፡ በተፈታች ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታውን ፡ በዛ ብህ ፡ እንደ ፡ ልግዱ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ አጥሩ ፡ ውስጥ ፡ ሲዘ ዋወር ፡ ቆይቶ ፡ ሲለለቸው ፡ እቤቱ ፡ ጥግ ፡ በተጋደመው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ ተቀመጠና ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ።

“ ምን ፡ እግኝቶዋቸው ፡ ይሆን ፡ እስካሁን ፡ የቆዩ ? ይህን ፡ ያክል ፡ አምሽተው ፡ አያውቁም ! ” አለ ፡ ብቻውን ፡ እግንዱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ።

ጉዱ ፡ ካሳ ፡ በጊዜ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዮ ፡ ልምጣ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አልተመለሰም ፡ እውነትም ፡ በዛብህ ፡ እዚያ ፡ ቤት ፡ ከተቀመጠ ፡ ጀምሮ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ እውጭ ፡ አምሽቶ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ካጥር ፡ ውጭ ፡ የግር ፡ ዳና ፡ የሰማ ፡ መሰለውና ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንድ ፡ ጆሮውን ፡ ዳናውን ፡ ወደለማበት ፡ ደቅኖ ፡ ቆይቶ ፡ በሁዋላ ፡ ወዳጥሩ ፡ በር ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሲገባ ፡ አዩ ። ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ነው ።

“ ማነህ ፡ አንተ ? ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እጥግ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ የተቀመጠውን ፡ ሰው ፡ በሩቁ ፡ ሲያይ ።

“ እኔ ፡ በዛብህ ፡ ነኝ ፡ ጤና ፡ ይስጥልኝ ! ምነው ፡ በጤ ናዎ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ያመሹ ? ”

“ የምሰራች ! ”

“ ተፈታች ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ከተቀመጠበት ፡ እንደ ፡ ኩዋስ ፡ ነጥሮ ፡ ተነስቶ ። ጨኸቱ ፡ በሩቅ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ ይቀሰቅስ ፡ ነበር ።

“ ቀስ ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ በል ! ና ፡ እቤት ፡ እንግባ ! ” አለና ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ በዛብህ ፡ እዩሮጠ ፡ ገብቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የቀኝ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግራ ፡ ጉልበቱን ፡ እዩ መላለስ ፡ ይስም ፡ ጀመር ።

ከዚያ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ እንደ ፡ ምንም ፡ ታግሎ ፡ ቀና ፡ ሲያ ደርገው ፡ የደስታው ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ጸደቀች ፡ ነፍስ ፡ የሚያ ደርገውንም ፡ የሚለውንም ፡ አሳጥቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዩወረደ ፡ “ ተመስገን ፡ ተመስገን ፡

ተመስገን ---- ሲል ፡ ሁኔታውን ፡ ሁሉ ፡ ተመልክቶ ፡ ጉዱ ፡ ካሳም ፡ ልቅሶ ፡ መጣበትና ፡ እንባት ፡ ላንባት ፡ ተያይዘው ፡ እዩሳቁ ፡ ብዙ ፡ እንባ ፡ አፈሰሱ ።

“ ለመሆኑ ፡ ማን ፡ ነገረዎ ? ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ሰውነቱ ፡ ትንሽ ፡ ጸጥ ፡ ካለ ፡ በሁዋላ ።

“ ወዳፋፍ ፡ ሄጄ ፡ ነፋስ ፡ ተቀብዬ ፡ ስመለስ ፡ ሀብትሽን ፡ ውሀ ፡ ልትቀዳ ፡ ስትሄድ ፡ አግኝት ፡ ነገረችኝና ፡ ሄጄ ፡ እዩ ሁዋት ። ”

“ ሰብለን ፡ ራስዎ ፡ ሄደው ፡ እዩዋት ? ”

“አምን ፡ እዩሁዋት ፡”

“ እንዴት ፡ ናት ? ከስታለች ? ትናገራለች ? ትስታለች ? ”

“ከስታለች ፡ ዝርጥታለች ፤ ምንዋም ፡ ምንዋ ፡ ሰብለን ፡ አይመስል ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ባዘን ፡ ድምጽ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ። በዛብህም ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ።

“ ለመሆኑሳ ፡ እንዴት --- ፈቱዋት ? እስማት ፡ አብነት ፡ ይሉት ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ? አሰ ፡ በዛብህ ፡ ሁሉ ቱም ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ብዙ ፡ ከቆዩ ፡ በሁዋላ ።

“ ተፈታ ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወደ ፡ በዛብህ ፡ ቀና ፡ አለና ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

“ እንዴት ? ምኑ ? ”

“አንተ ፡ ያደረግህባት ፡ አስማት ! ”

በዛብህ ፡ ከድንጋጤም ፡ ከመገረምም ፡ ብዛት ፡ የሚና ገረው ፡ ቅጡ ፡ ጠፍቶት ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ ጉዱ ፡ ካሳን ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

“ አስማቱም ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ያልተለመደና ፡ የጎጃም ፡ መፍትሄ ፡ ስራይ ፡ አዋቂ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈታው ፡ የማይችል ፡ ነበረ ፡ አሉ ! ” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ አሁንም ፡ ያሽሙር ፡ ፍር ጥምታ ፡ ፍርጥም ፡ ብሎ ።

“እንግዲያ ፡ ማን ፡ ፈታው?”

“ካባይ ፡ ማዶ ፡ ከጉድሩ ፡ የመጡ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት፡ የሚባሉ ፡ ስልብ!”

"በዚህ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ እንዴት - - - አድርገው ፡ ከጉድሩ ፡ ማስመጣት ፡ ቻሉ ?"

"እዚህ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ግሁስ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ ሰውን ፡ ሊዘርፉ ፡ ቆይተዋል ፡ እንጂ!"

አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሀይማኖት ! እኒህ - - - ዘግተው ፡ ይኖራሉ ፡ የሚባሉት?"

" አ --- ዎ! ዘግተው ፡ ይኖራሉ ፡ የሚባሉት!"

"እሳቸው ፡ ናቸው ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ ያልተሰመደ ፡ በሙሉ ፡ ጎጃም ፡ የማይፈታ ፡ አስማት ---------- የሚሉት ? "

"እሳቸው ፡ ናቸው!" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፤ አፉቱ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ በነበረው ፡ አሽሙር ፡ ፈንታ ፡ ቁጣ ፡ ተተክቶ ፡ አይኑ፡ በቅጥበት፡ ቀልቶ ::

"እየውልህ! ቤተ ፡ እግዚአብሄራችን ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ሽፍቶች ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ዘራፊዎች ፡ ዋሻ ፡ ሆነች! እየውልህ! ከካህናቶቻችን ፡ ከሀዋርያቶቻችን ፡ የሚበዙት ፡ ካስቆች ፡ ጀምሮ ፡ በመነኮሳቱ ፡ አልፎ ፡ እስከ ፡ ተራ ፡ ደብተሮች ፡ እስከ ፡ ዲያቆናቱ ፡ ድረስ ፡ አንዱ ፡ አስማት ፡ አድራጊ ፡ አንዱ ፡ አስማት፡ ፈቺ ፡ ሌላው ፡ ጋኔን ፡ ስቦ ፡ አምጪ ፡ ሌላው ፡ አስወጪ ፡ አንዱ ፡ መቅሰፍት ፡ አምጪ ፡ ሌላው ፡ ምህረት ፡ አሰጪ ፡ ነን ፡ እያሉ ፡ ውሸታቸውን ፡ በዬጥምጥማቸው ፡ በዬቆባቸው ፡ በዬደበሎዋቸው ፡ ሸሽገው ፡ ሊመሩት ፡ ሊያስተምሩት ፡ በተሰጣቸው ፡ መንጋ ፡ የሚጫወቱ ፡ ናቸው! ታዲያ ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ማህበር ተኛ ፡ ሆኖ ፡ ባንድ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሄርን ፡ መጥራት ፡ በተቀደሰ ፡ ስሙ ፡ ማፌዝ ፡ አይደለም ? እየውልህ! ይህ ፡ ነው ፡ ክምወዳት ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሄር ፡ ያራቀኝ! ሰው ፡ የሚለው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እውነቱ ፡ ይህ ፡ ነው :: አሁን ፡ አንተ ፡ በራስህ ፡ ባይ ደርስ ፡ ኖሮ ፡ እኒህ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ያደርጋሉ ፡ ብዬ ፡ ብነግርህ ፡ አታምንም ፡ ነበር :: ታምን ፡ ኖሮዋል?"

"ካጭራሽ ፡ አላምንም ፡ ነበር ፡"

"እየውልህ ፡ ብዙዎቹ ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ::"

"ታዲያኮ ፡ እንደሰም ፡ ያሰ ፡ ሰው ፡ በካህናቱ ፡ ክፋ ፡ ስራ ፡ ተቀይሞ ፡ ከመሸሸ ፡ እመህክላቸው ፡ ሆነው ፡ ለነሱም ፡ ለሚያታ

ልሉት ፡ ህዝብም ፡ ቢሰብኩ ፡ በጠቅላላው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልካም ፡ ነበር!"

"ያልጀመርሁት ፡ መሰለህ? ለምናገረው ፡ ሰው ፡ ዋጋ ፡ እንዳይሰጠው ፡ እብድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስወሩብኝ ፤ እብዱ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ ያሰጠኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።"

በዛብህ ፡ አንገቱን ፡ ደፋ ፡ አደረገና ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆይቶ ፡ "እንኩዋን ፡ ተፈታች ፡ እንጂ ፡ ግዴለም!" አለ ።

በበነጋው ፡ ጥዋት ፡ ቡና ፡ ተጠጥቶ ፡ እንቆጳም ፡ ሌሎችም ፡ ሁሉ ፡ ወደዱስራቸው ፡ ከተሰማሩ ፡ በሁዋላ ፡

"ምን ፡ አሰብህ ? በዛብህ ?" አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

"እንዴት? ስለምኑ?"

"እንግዲህ ፡ ሰብለ ፡ ተፈታች ፤ ስለራስህ ፡ ምን ፡ ለማድረግ፡ ታስባለህ ፡ ማለቴ ፡ ነው!"

"ማሰብማ ፡ ሌሊቱን ፡ እንቅልፍ ፡ አጥቼ ፡ ሳስብ ፡ ነው ፡ ያደርሁ ፤ ብቻ ፡ የምጨብጠውን ፡ ነገር ፡ አጥቼ ፡ ተቸገርሁ ፡ እንጂ!"

"የሚሻል ፡ የመሰለኝን ፡ እኔ ፡ ልንገርህ?"

"ምን ፡ ይሻለኛል? አስቲ ፡ ይንገሩኝ!"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ! ወደዚያ ፡ መሄድህ ፡ ነው ፡ የሚሻለው ።"

"እንዴት?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ደንግጦ ።

"እስከ ፡ መቼ ፡ እዚህ ፡ ተሸሽገህ ፡ መቀመጥ ፡ ትችላለህ? ለመቀመጥ ፡ ብትችልስ ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ?"

"እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፤ አንገቱን ፡ ደፍቶ፡ ሲያስብ ፡ ቆይቶ ። "ብቻ ፡ አዲስ ፡ አበባስ ፡ ሄጄ ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ? ይህን ፡ አደርጋለሁ ፡ የምለውን ፡ ነገርኮ ፡ አጣሁ!"

"አዲስ ፡ አበባ ፡ ሂድ ፡ ያልሁበትን ፡ ምክናያት ፡ ልንገርህ? አንደኛ ፡ በጎጃም ፡ መሬት ፡ መኖርህ ፡ ከታወቀ ፡ ፊታውራሪ ፡ መከታተላቸው ፡ ስለማይቀር ፡ አንተም ፡ ሰብለም ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የምትኖሩ ። ሁለተኛ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደህ ፡ ስራ ፡ የያዝህ ፡ እንደሆነ ፡ አሳብህ ፡ በስራህም ፤ በሌላውም - - - መህክል ፡ ይከፍሩልና ፡ ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ እዚህ ፡ የደ

ረሰውን - - - - - ሁሉ ፡ መርሳት ፡ ትችል ፡ ይሆናል ። እንዲያ ውም ፡ ግልጥ ፡ አድርጌ ፡ ልንገርህ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ይዘህ ፡ ልብህ፡ የሚደነግጥላት ፡ ልጅ ፡ ብታገኝ ፡ ቶሎ ፡ እንድታገባ ፡ ነው ፡ የም መክርህ ፡"

እሱን ፡ እንኩዋ ፡ ይተውት ! ሰብለ ፡ ከቀረች ፡ እመነኩሳ ለሁ ፡ እንጂ ፡ ምሽት ፡ አላገባም !"

"ተሳስተሀል ! እግዚአብሄር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሴት ፡ የፈ ጠረ ፡ ሰብለን ፡ ብቻ ፡ ነው ?"

"ሌትግ ፡ ሞልቶዋል ! ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ባልገናኝና ፡ እስ ዋን ፡ ባላውቅ ፡ ኖሮ ፡ አንድዋን ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ አግብቼ ፡ ለመ ኖር ፡ ምኞቴ ፡ ነበር ። አገሬንም ፡ የለቀቅሁ ፡ በቀደም ፡ እንዳጫወ ትሁዎ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ቤቱ ፡ ሰርቼ ፡ ለመኖር ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሄር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ለዚህ ፡ አልመደበኝም ፡ መሰለኝ፡ ከስዋ ፡ ጋር ፡ አገናኘኝ ። ከንግዲህ ፡ ወዲያስ ፡ አላገባም ። ሌላ ፡ ምሽት ፡ ከግግባቱ ፡ ላጭር ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እስዋ ፡ የሰጠችኝን፡ ደስታ ፡ እያሰብሁ ፡ መቀመጡ ፡ ይሻለኛል !" አለ ፡ በዛብህ ፡ እን ባው ፡ ባይኑ ፡ ሞልቶ ።

"ይገርማል ! ለካ ፡ ክፉም ፡ ሆነ ፡ በጎ ፡ የሚሰሩ ፡ ሰዎች ፡ መሳ ሪያዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሰራተኛው ፡ እግዚአብሄር ፡ ስለሆነ ፡ እነሱን ፡ መጥላቱና ፡ ማጣቱ ፡ ወይም ፡ መውደዱና ፡ ማመስገኑ ፡ ከንቱ ፡ ነው ! እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ባይኖሩ ፡ ያ ፡ ክፉ ፡ የተሰራበት፡ ወይም ፡ በጎ ፡ የተሰራለት ፡ ዞሮ ፡ ዞሮ ፡ ክፉውን ፡ ወይም ፡ በጎ ውን ፡ በሌላ ፡ አማካይነት ፡ አያጣውም ፡ ማለት ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ቀጠለና ።

" እንዴት ?"

" በቀደም ፡ እንደነገርሁዎ ፡ እናቴ ፡ ምሽት ፡ ሳላገባ ፤ በድ ንግልና ፡ ታቦት ፡ እንዳገለግል ፡ በስእለት ፡ ስለሰጠችኝ ፡ በስዋ ፡ አገኘ ፡ ከታሰርሁበት ፡ አምልጡ ፡ ምሽት ፡ አግብቼ ፡ ለመኖር፡ ነበር አገሬን ፡ የለቀቅሁ ። ይዩት ፡ አሁን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደ ዚያው ፡ ጥንት ፡ ወደተመደበልኝ ፡ ህይወቴ ፡ መመለሴ ፡ ነው !"

" እስቲ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ በዛብህ !"

"መቸም ፡ ዲማ ፡ ከመጣህ ፡ ጀምሮ ፡ ሰብለን ፡ ታውቃ ታለህ ! መቸ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ከተፈጠረው ፡ ሴት፡ ሁሉ ፡ የተለየች ፡ ሆና ፡ ትታይህ ፡ የጀመረች ?"

"መጀመሪያ ፡ ሳያትም ፡ ልቤ ፡ ደንገጥ ፡ ብሎዋል ፡ ብቻ ፡ እሱ ፡ መልከ ፡ ቀና ፡ ሴት ፡ ሲታይ ፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ያክል ነው ። እንጃ --- እንዲያውም ፡ ትንሽ ፡ እፈራት ፡ ነበር ፡ መሰለኝ። የቀረው ፡ አሁን ፡ በቅርቡ --ነው ።"

"እየውልህ! ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መተዋወቃችሁ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጉዋደ ኝነታችሁ ፡ ጭዋታችሁ ፡ መላፋታችሁ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ መጨረሻ ፡ አደረሳችሁበት ፡ ላይ ፡ አደረሳችሁ ! ከዚያ ፡ በጣም ፡ ተዋደዳችሁ ! ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ እንደሰዋ ፡ በቅርብ ፡ ካወቅህቸው ፡ ከብዙዎቹ ፡ መሀከል ፡ አንድ ፡ የምትወዳት ፡ የም ታጣ ፡ ይመስልሃል ?"

"የሰም ፡ አላገኝም ፤ አለቃ ! ሰብለ ፡ ልዩ ፡ ናት ። ከሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ናት ! ምሽትም ፡ ባላገባ ፡ ብዙ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ አው ቃለሁ ። ታዲያ ፡ የማውቃቸው ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ሁሉ ፡ የሚዋ ደዱትም ፡ ባሳብ ፡ ባለመሰማማት ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ጭቅጭቅ፡ አያጣቸውም ። ይገርምዎታል ፡ ሰብለና ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነፍስ፡ እንደ ፡ ተጋራን ፡ ሁሉ ፡ እስዋ ፡ ያሰበችውን ፡ እኔ ፡ ስናገር ፡ እኔ ፡ ያሰብሁትን ፡ እስዋ ፡ ስትናገር ፡ እንገኝና ፡ ተያይዘን ፡ መሳሳቅ ፡ ብቻ ፡ መደሰት ፡ ብቻ ፡ ነው ! ምነው ፡ አብረን --- እንዲህ ፡ ስን ሆን ፡ ቢያዩን ፡ ኖሮ ! አለና ፡ በዛብህ ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ መቅረቱ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡ እንባው ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።

"ግሩም ፡ ነው ! አንተም ፡ እንደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያሰ ፡ አባት ፡ ዚኖርህ ፡ ሰብለ ፡ አስማት ፡ አድርጋበታለች ፡ ትባል ፡ ነበር ።"

" ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አይንዋን ፡ የማይበት ፡ ዘዴ ፡ የሚገኝ ፡ ይመስልዎታል ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆይተው ።

" አልነገርሁህም ፡ መሰለኝ ፤ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትኮ ፡ ጠባቂ ፡ ጭምር ፡ እንዲሆኑ ፡ ተቀጥረዋል !"

" አምላ ፡ ብር ፡ አለኝ ፤ እሱን ፡ ብሰጣቸውና ፡ አንድ ፡ ማታ፡

አስገብተውኝ ፡ አይቻት ፡ ብሄድ --- እሺ ፡ የሚሉ ፡ አይመስል ዎትም ?

“ እንደሳቸው ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሴት ፡ ስመጠበቅ ፡ የሚመ ረጡ ፡ በጥብቅነታቸው ፡ የታወቁ ፡ በመሆናቸው ፡ መሆኑን ፡ አታውቅም ?”

“ ጥብቆችና ፡ ታማኞች ፡ ናቸው ፡ ሲባሉስ ፡ እሰማለሁ ፤ ብቻ ፡ ተሰናብቼ ፡ ስመሄድ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ልስጥ ፡ ስል ፡ ገንዘቡ ፡ ያጉዋጉዋቸው ፡ ይሆናል ፤ ወዲያውም ፡ እምነት ፡ አጎደሉ ፡ የሚ ያሰኝ ፡ ነገር ፡ አይኖርም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ !”

“እምነት ፡ እንኩዋ ፡ አይደለም ፤ ቅናት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ቢወዱ ፡ ቅናታቸው ፡ ከገንዘብ ፡ ፍቅራቸው ፡ ይበልጣል ። ዝም ፡ ብለህ ፡ ሂድ ፡ እንዳያስይዙህ ። ሁላችንም ፡ ደ ህና ፡ ከሆን ፤ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ካገኘሁ ፤ ከቻልሁ --- ሰብለን ፡ ስርቄ ፡ አንተ ፡ ባለህበት ፡ ስማድረስ ፡ መሞከሬ ፡ አይቀርም ፤ ብቻ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ። እዚያ ፡ እንደ ፡ ደረስህ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ያዝና፡ የተቀመጥህበትን ፡ ቦታ ፡ አስታውቀኝ ።”

በዛብህ ፡ እንባው ፡ በግራ ፡ ቀኝ ፡ ጉንጩ ፡ እዬወረደ ፡ ተነ ስቶ ፡ የጉዱ ፡ ካሳን ፡ ጉልበት ፡ ሳመ ።

“ግዴለህም ፡ አፈር ፡ ካልተጫነኝ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሰብለን ፡ በጅህ ፡ አገባታለሁ ! ብቻ ፡ ቶሎ ፡ ሂድና ፡ ስራ ፡ ያዝ ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ ስራ ፡ ያዝ !” አለ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ።

ምእራፍ ፡ ፳፱

አዲስ ፡ አበባ ፡

በዛብህ ፡ ከጉዱ ፡ ካሳ ፡ ከግራ ፡ ጌታ ፡ ቀለመወርቅና ፡ ከእዝራ ፡ ጋር ፡ ከዲግ ፡ በጨለማ ፡ ወጥቶ ፡ ድምጽ ፡ የሰማ ፡ በመሰለው ፡ ቁጥር ፡ አሳቡ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እዬተጎተተ ፡ ተራ ሮች ፡ እስኪጋርዱት ፡ ድረስ ፡ በዬደቂቃው ፡ ዲግን ፡ እዬዞረ ፡ እያዬ ፡ እሳይ ፡ ደረሰ ። ከዚያ ፡ ከወዳጆቹ ፡ በንባ ፡ ተሰነባብቶ ፡ ከሞጣ ፡ ነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ገሳ ።

ካሳይ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አሸር ፡ ቀን ፡ ሲጉዋዝ ፡ ስላዲስ ፡ አበባ ፡ የነገሩት ፡ ወሬ ፡ እስበሱ ፡ የሚ ማታኖ ፡ ማነኛውን ፡ መያዝ ፡ የሚያስችግር ፡ ስለነበረ ፡ ሰግቶ ፡ ነበር ።

“ ስራ ፡ ለሚያውቅ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ እስኪላጥ ፡ ቢሄዱ ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ የመሰለ ፡ አገር ፡ ይገኛል ፡ ብለህ ፡ አታስብ !” ይለዋል ፡ አንዱ ።

“ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሌቦች ፡ አገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰርተው ፡ የሚያድሩ ፡ ሰዎች ፡ አገር ፡ አይደለም ! ያዲስ ፡ አበባ ፡ ሌባ ፡ እንዳገርህ ፡ ሌባ ፡ ጨለማ ፡ ለብሶ ፡ የሚሰርቅ ፡ መሰለህ ? የለም ፡ አይንህ ፡ እያዬ ፡ ብርሀን ፡ ከኪስህ ፡ አውጥቶ ፡ ይወስደዋል ! እንዲያው ፡ እንጂ ! ያፍዝ ፡ ያደንግዝ ፡ አለው ፡ መሰለኝ !” ይለዋል ፡ ሌላው ።

“ አ --- ! ጽህፈት ፡ የሚያውቅማ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ልፋፈ ፡ ጽድቁንና ፡ ከታቡን ፡ እየጻፈ ፡ ብሩን ፡ በቱና ፡ መስፈር ፡ ነው !” ይለዋል ፡ አንዱ ።

“ ምን ፡ ዛሬማ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ረከሰ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ! ድሮ ፡ አንድ ፡ ገድል ፡ ወይም ፡ ታምር ፡ ጽፈህ ፡ ላንድ ፡ መኮዋንንት ፡ ብትሰጥ ፡ አንድ ፡ ጠብደል ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ እምላ ፡ ስድሳ ፡ ብር ፡ ታገኝ ፡ ነበር ፡ ዛሬስ --- ካንድ ፡ ሊቅ ፡

አንድ ፡ የኔ ፡ ብጤ ፡ ደንቆሮ ፡ ይሻላል ፡ እንጨቱን ፡ ይሁን ፡ ድንጋዩን ፡ ወይም ፡ ውሀውን ፡ ተሸክሞ ፡ ሆዱን ፡ ሞልቶ ፡ ያድራል ! ” ይለዋል ፡ ሌላው ።

“ አዲስ ፡ አበባ ፡ የማውቀው ፡ ሰው ፡ የለኝም ፡ ምን ፡ ባደርግ ፡ የሚሻለኝ ፡ ይመስልዎታል ? እስቲ ፡ ይምከሩኝ ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሊገቡ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀራቸው ፡ ሱሉልታ ፡ በሰፈሩበት ፡ ተቀምጠው ፡ ሲጫወቱ ።

“ ገንዘብ ፡ ካለህ ፡ አትቸገርም ፡ ገንዘብም ፡ የምታውቀው ፡ ሰውም ፡ የሌለህ ፡ እንደሆን ፡ ነው ፡ ችግሩ ! እስቲ ---- ለማናቸውም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ጉለሌ ፡ ሰፈርና ፡ አንተም ፡ እኛም ፡ ስራ ፡ እስክታገኝ ፡ የምትቀይበት ፡ ሰው ፡ እንፈልጋለን ። ” አሉ ፡ ነጋድራስ ።

“ ገንዘብስ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ ያነጣጠሙኝ ፡ ወዳጆች ፡ አዋጥተው ፡ የሰጡኝ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አለኝ ። ”

“ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ካለህማ ፡ ግለፊያ ፡ ቤት ፡ ተከራይተህ ፡ ግለፊያ ፡ ቀላቢ ፡ ቀጥረህ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያቆይሀል ። ብቻ ፡ ቢሆንም ፡ አገሩን ፡ እስክትለምደው ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ብትቆይ ፡ ይሻላል ። ገንዘብህም ፡ እንዳይጠፋብህ ፡ መጠንቀቅ ፡ ነው ። ”

በዛብህ ፡ ሰፈሩን ፡ ጉለሌ ፡ ከነጋዴዎች ፡ ጋር ፡ አድርጎ ፡ ጥቂት ፡ አብሮዋቸው ፡ ይወጣና ፡ አራዳ ፡ ሲደርስ ፡ ተለይቶዋቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ የሚሸጥባቸውን ፡ ሱቆች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ትልልቅ ፡ ግቢዎችንና ፡ አደባባዮችን ፡ እዩ ዞረ ፡ ሲያይ ፡ ውሎ ፡ ግቷ ፡ ደከሞት ፡ ይመለሳል ። ከገንዘቡ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ የቀረውን ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ እንዲይዙለት ፡ ስለሰጠ ፡ አሰረቃለሁ ፡ ወይም ፡ እቀማለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚሰጋበት ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። ነገር ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ቢሄዱት ፡ የማያልቅ ፡ ትልቅ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የህዝቡ ፡ ኑሮ ፡ ልማዱ ፡ እንዲያው ፡ በጠቅላላው ፡ ምኑም ፡ ምኑ ፡ ጎጃምን ፡ እስኪለቅ ፡ ከሚያውቃቸው ፡ እንደ ፡ ሞጣ ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ዲማ ፡ ካሉት ፡ ከተሞች ፡ በጭራሽ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ ስለታዩው ፡ ለጊዜው ፡ ድንግርግር ፡ አለው ።

ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ባንድ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቁሞንቁሞ ፡ መነገሩ ፡ አስገረመው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ አግርኛ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ስብሩም ፡ ሆነ ፡ ቃሉ ፡ አግርኛ ፡ አልመስለው ፡ አለ ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ልማዱን ፡ አለማወቁ ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ ይጥለኝ ፡ ይሆን ፡ እያለ ፡ ይሰጋ ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ኩታውን ፡ ተከናንቦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሊሄድ ፡ ገና ፡ ከሰፈሩ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡ “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ ክንንቡን ፡ አውርዶ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ልጄት ፡ አደርክ ? ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አሰኘ ። በዛብህ ፡ ግን ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ሰውዬው ፡ ገርሞት ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ በዛብህን ፡ እስኪርቅ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ጉድ ፡ ሲመለከተው ፡ ቆይቶ ፡ እሱም ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ መንገደኛ ፡ አገኘና ፡ አሁንም ፡ እንደፊተኛው ፡ ክንንቡን ፡ አውርዶ ፡ “ እንዴት ፡ አደሩ ፡ ጌታው ! ” አለ ።

“ እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ” አለ ፡ መንገደኛው ፡ እሱም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ መንገደኛ ፡ ምን ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቆም ፡ አለና ። በዛብህ ፡ አሁንም ፡ ኩታውን ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ገፋ ፡ አድርጎ ፡ መንገዱን ፡ ሊቀጥል ፡ ሲል ፡-

“ የት ፡ ታእኛለህ ? እባክህ ! ” አሰው ፡ መንገደኛው ።

“ እሺ ፡ አላውቅዎም ፡ ጌታው ! ” አለ ፡ በዛብህ ፡ እንደ ፡ መፍራት ፡ ብሎ ።

“ ታዲያ ፡ ሳታእኝ ፡ ነው --- እንዲሁ ፡ ተነሰተህ ፡ እንዴት አደርክ ፡ ያልከኝ ?”

“ እሺ ፡ አላውቅዎም ፡ የእግዚአብሄርን ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ያነሳል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ።”

“ይህ ፡ አታላይ ፡ መልቲ ፡ እድፍ ፡ ዉርእ ፡ ብለብስ ፡ ባላ

ገር ፡ መሰልኩህ ?''

'' እረ ፡ አኔ ---''

''አትኬድም ፡ አሁን ? አንት ፡ ሽአባ ! እንዳንት ፡ ያለውን ፡ ሌባ ፡ የማላእ ፡ መሰለህ ? አሁን ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቼ ፡ አስእፈድድህ ፡ ነበር !''

በዛብህ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ሰውዬው ፡ የተናገረውን ፡ ቃል በሙሉ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ባይችል ፡ ዘጠቅላላው ፡ አሳቡ ፡ ስለ ገባው ፡ ደንግጠ ፡ መንገደኛው ፡ የተቆጣበትን ፡ ምክናያት ፡ ግን ፡ ባለማወቁ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፡ እዘያ ፡ ቆሞ ፡ ሲሳደብ ፡ ትቶት ፡ ሽሽ። ከዘያ ፡ የከተማው ፡ መንገድ ፡ ሁሉ ፡ እዘያ ፡ የገጠመውን ፡ ችግር፡ ይዞ ፡ የሚቆዬው ፡ ስለመሰለው ፡ በመንገድ ፡ የሚያገኘው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘበኛ ፡ ጠርቶ ፡ የሚያሳስረው ፡ ስለመሰለው ፡ ወደ ፡ ከተማ፡ መሄዱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ተመለሰና ፡ ተሸሽጎ ፡ ድምጽ ፡ በሰማ ፡ ቁጥር ፡ ካሁን ፡ አሁን ፡ ዘበኛ ፡ መጣብኝ ፡ እያለ ፡ ሲሸበር ፡ ዋለ ። ግታ ፡ ነጋድራስ ፡ ሁነኛውና ፡ ጉዋደኞቻቸው ፡ ከገዘያ ፡ ሲመለሱ ፡ የደረሰዙትን ፡ ሲነግራቸው ፡ ገዜ ፡ ይሰቁ ፡ ጀመር ።

'' አዬህ ? እዘህ ፡ አገር ፡ እንዳገራችን ፡ በመንገድ ፡ ለምታገኘው ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስላምታ ፡ መስጠት ፡ የለብህም !'' አሉ ፡ ነጋድራስ ።

'' እንዴት ? እንዲየው ፡ እንዲሁ ፡ እንደተቀያዬሙ ፡ ሁሉ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መተላለፍ ፡ ነው ? ''

'' ልማድ ፡ ሆኖ ፡ ሰው ፡ ለሚያውቀው ፡ ሰው ፡ ስላምታ ፡ አይሰጥም ። መንገድ ፡ ወይም ፡ ቦታ ፡ ሲጠፋህ ፡ ብቻ ፡ የማታውቀው ፡ ሰው ፡ ዘሆንም ፡ ስላምታ ፡ ሰጥተህ ፡ የጠፋህን ፡ ብትጠይቅ ፡ ግዴለም ። ያለዘያ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማለፍ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ጠንካራ ፡ ጸሀይ ፡ ወይም ፡ ዝናብ ፡ ካልሆነ ፡ ተከናንቦ ፡ መሄድ ፡ እዘህ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ አይደለም ። ያላንድ ፡ ምክናያት ፡ ተከናንበው ፡ የሚሄዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊታቸው ፡ እንዲታይ ፡ የማይፈልጉ ፡ ሌቦች ፡ ወይም ፡ ቀማኞች ፡ ናቸው ። ስለዘህ ፡ በደህና ፡ ገዜ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ ስትሰጥ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ ትመስለዋለህ ። ለዘህ ፡ ነው ፡ ሰውዬው ፡ የተቆጣ ።''

''ግሩም ፡ ነው ! እንግዲህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቀዋንቀዋና ፡ ልማድ ፡ አስካጠና ፡ ብዙ ፡ ገዜ ፡ መፍጀት ፡ ስለማያቀር ፡ ስራ ፡ ፈልጌ ፡ ባገኝም ፡ ከዘያ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ማለት። ነው !'' አለ ፡ ዘዛ ብህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቁ ፡ ቶሎ ፡ ስራ ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፡ መሰናክል ፡ ስለመሰለው ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ተስፋ ፡ እንደሰጠው ፡ ሰብለን ፡ ያመጣለት ፡ እንደሆነ ፡እብር፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ መሆኑ ፡ ትገ ፡ ብሎት ፡ ገም ፡ ብሎ ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ሲያስብ ፡ ቆዬና ፡

'' የለም ፡ አይዘህ ፡ ሁሉንም ፡ አሁን ፡ ትለምደዋለህ ። ቁዋንቁዋው ፡ መቸም ፡ ያው ፡ የምታውቀው ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ 'ቀን' ፡ በ'አ' ፡ 'ዘን' በ'ዝ' ፡ እዬሰወጡ ፡ ስለሚናገሩና ፡ ጀሮህ፡ ስላለመደው ፡ ለጊዜው ፡ ልዩ ፡ ቁዋንቁዋ ፡ ይመስላል ። '' አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ፍረጥም ፡ ብለው ።

'እሺ ፡ ቁዋንቁዋውስ ፡ ይሁን ፡ ልማዱ ፡ እስኪታወቅ ፡ ብዙ ፡ ገዜ ፡ አይፈጅም ? ለምሳሌ ፡ የግዜርን ፡ ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ነውር ፡ ሆኖ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አታላይ ፡ የሚያስመስልና ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ የሚያጣላ ፡ ከሆነ ፡ ነውር ፡ ያልሆነው ፡ ምንድር ፡ ነው ? እንዴትስ ፡ አድርጎ ፡ ቀርቦ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ለመተዋወቅና ስራ ፡ ተጠያቂ ፡ ግግኘት ፡ ይቻላል ?''

'' አይዞህ ፡ አትፍራ ፡ ልማዱም ፡ ዘሆን ፡ ይሆን ፡ ያክል ፡ ካገራችን ፡ የተለዬ ፡ አያደለም ፡ ትንሽ ፡ ብቻ ፡ ነቃ ፡ ማለት ፡ ነው፡ የሚያስፈልግ ። ሰላምታ ፡ መስጠት ፡ ለምን ፡ አታላይ ፡ አስመስሎ፡ አሳዬ ፡ ለምትለው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከያገሩ ፡ ብዙ ፡ አታላዮች ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ከተማ ፡ ነው ፡ አንዳንዶቹ ፡ አታላዮችም ፡ ከነ ተና ፡ ከኔ ፡ አገር ፡ የሚመጡ ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያሉት፡ ሰዎች ፡ እንግዳ ፡ ወይም ፡ የሚታለል ፡ ሰው ፡ ያዩ ፡ ሲመስላቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ሰላምታ ፡ በመስጠት ፡ ቀጥሎም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የማ ታለያ ፡ መንገድ ፡ ደጎችና ፡ ረዳቶች ፡ በመምሰል ፡ ቀርበው ፡ የስ ርቆት ፡ የቅምያና ፡ ሌላም ፡ የወንጀል ፡ ስራቸውን ፡ የሚፈጽሙ ፡ መሆናቸው ፡ ከብዙ ፡ ገዜ ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ሆኖዋል ። ስለ ዚህ ፡ ለማታውቀው ፡ ሰው ፡ ተከናንበህ ፡ ሄደህ ፡ ሰላምታ ፡ ስት

ሰጥ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ተጠራጥሮ ፡ ቢቆጣ ፡ እያግረምህ ። ይልቅ ፡ ቅድም እንዳልኩህ ፡ አለመፍራት ፡ ነው ። ስትሰጋኝ ፡ የንግድነት ፡ መልክ ፡ ስታሳያ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ እይን ፡ ይከታተልህና ፡ አንተም ፡ በበኩልህ ፡ ያን ፡ ታስያ ፡ ነውር ፡ የሰራህ ፡ መስሎህ ፡ ፋራት ፡ አያ ለያህም ፡ ስትባንን ፡ ትኖራለህ ።''

ኒጋድራስ ፡ ሁኔኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ከተገናኙ ፡ ጀምረው ፡ ትህትናውንና ፡ በጣም ፡ የታረመ ፡ አመል ፡ ያሰው ፡ መሆኑን ፡ በማየታቸው ፡ ይወዱት ፡ ስለነበረ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ኑሮ ፡ ያን፡ ያክል ፡ ሲፈራው ፡ እንደማይጎዳና ፡ በራሱ ፡ እምነት ፡ እንዲኖረው፡ በየጊዜው ፡ እዩመከሩ ፡ ያደፋፍሩት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚኖሩ ፡ አንዳንድ ፡ የሚያውቋቸው ፡ ደህና ፡ ሰዎች ፡ አስተዋወቁት ። ብቻ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሆኖ ፡ በዛብህ ፡ ከመንጋዋ ፡ ለይተው ፡ ከንግዳ ፡ መንጋ ፡ እንደ ፡ ጨመርዋት ፡ ላም ፡ መቡዋ ዘዙና ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ብቸኛነት ፡ የሚሰማው ፡ መሆኑ ፡ አልቀረም ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ቲቀምጦ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚታዩው ፡ የሰብስ ፡ መልክ ፡ የሚሰማው ፡ የሰብለ ፡ ድምጽ ፡ የሚታሰበው ፡ ሰብለን ፡ አስኮብልሎ ፡ ለማምጣት ፡ ያቀ ደው ፡ እቅድና ፡ በመጨረሻ ፡ በስዋ ፡ ፈንታ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ የሰጠ ውን ፡ በጥርጣሬ ፡ የተከበበ ፡ ተሰፋ ፡ ይዞ ፡ መምጣቱ ፡ ነበር ። ''ሀላችንም ፡ ደህና ፡ ከሆን ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ከተገኘ ፡ ከቻ ልሁ - - - - ሰብለን ፡ ሰርቄ ፡ በጅዘ ፡ ሳላገባት ፡ አልቀርም ፡'' ብሎ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሲሰናበተው ፡ የተናገረው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ መሀከል ፡ እንኮዋ ፡ በተቀመጠበት ፡ በጀሮው ፡ ውስዋ ፡ ጎልቶ ፡ ያሬሃዘትና ፡ ድንጉት ፡ አቀዋርጠ ፡''እግዚአብሄር ፡ ደህና ፡ ያድርግዎ ፡ የተመቸ ፡ አጋጣሚ ፡ ያምጣልዎ ፡ ያስችልዎ፡'' ሲል ፡ አብረውት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ይደነግጣሉ ፡ ወይም ፡ ሳይቶኛ ፡ ይቃዣል ፡ ብለው ፡ ያስቁበታል ።

''በዛብህ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማደም፡በተር ፡ ልብህ ፡ የሚያሰቀልልበት ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ያሰማኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንደነው ፡ ብለህ ፡ ብትጠይቀኝ ፡ ልነግርህ ፡ አልች ልም ። ብቻ ፡ ይህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በንቅልፉ ፡ ተነስቶ ፡ እንደ

ሚሄድ ፡ ሰው ፡ ፍዝዝ ፡ የሚያደርግህ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም፡ባፍላ ፡ ሞዋታ ፡ መሀከል ፡ የሚያቃዥህ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ቁዋንቁዋና ፡ ልማድ ፡ አለማወቅ ፡ ነው ፡ ብትለኝ ፡ የማልቀበለው ፡ ነገር ፡ ነው !'' አሉ ፡ ኒጋድራስ ፡ ሁኔኛው ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ሲጫወቱ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያልጠየቁትን ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ ሲደነግጥ ፡ አይተው ።

''ሌላ ፡ ምን ፡ ልቤ ፡ የሚያሰቀልልበት ፡ ነገር ፡ ይኖር፡መሰለዎ?'' አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ።

''ስሙን ፡ ጠርቸ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ልልህ ፡ አልችልም፡እንጂ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከመድረሳችንም ፡ በፊት ፡ ግና ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ተገና ኝተህ ፡ አሳይን ፡ ስትሻገር ፡ ጀምሮ ፡ የወለደችውን ፡ ሞጭቀው፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ እንዳስቀሩባት ፡ አራስ ፡ ላም ፡ ልብህ ፡ ወደ፡ሁዋላ፡ ሲጎትትና ፡ ሲያሰቀልል ፡ ደህና ፡ አድርጌ ፡ ተመልከቻለሁ ።''

''ካገራ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በመውጣቴ፡ ምናልባት፡በሌ ሎች ፡ ላይ ፡ የማይታይ ፡ ቅር፡ታ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አይተው፡ይሆናል።''

''ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከጎጃም ፡ ወጥቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ሲመጣ ፡ ያዩሁት ፡ ሰው ፡ አንተን ፡ ብቻ ፡ ይመስልሀል ?''

''አገሩን ፡ ለሁል ፡ ጊዜ ፡ ለቆ ፡ የሚሰደድ ፡ ማለቴ ፡ ነውኮ ፡ ደርሶ ፡ ተመላሽ ፡ አይደለም!''

''ቢሆንም ።''

''እንግዴህ ፡ እንደዬስሜት ፡ ቢሆን ፡ ነው ።''

''እይ ፡ በዛብህ! እኔኮ ፡ ጥሩ ፡ ኒጋዴ ፡ ነኝ! ጥሩ ፡ ኒጋዴና ፡ ጥሩ ፡ ጠንቁዋይ ፡ ግምት ፡ አዋቂዎች ፡ መሆናቸውን ፡ አታው ቅም?''

''እንዴት?''

''አዬህ? እገሌ ፡ ጥሩ ፡ ጠንቁዋይ ፡ ነው ፡ እዬተባለ ፡ የሚ ደነቀው ፡ ጠንቁዋይ ፡ ሁሉ ፡ እውነት ፡ ከዛርና ፡ ከ,ንኔን ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ ሰው ፡ የማያውቀውን ፡ ከነሱ ፡ እያገኘ ፡ አለመሆኑን ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ምናልባት ፡ አንተ ፡ ደብተራው ፡ ታውቅ ፡ ይሆናል፡ ካብዛኛው ፡ ሰው ፡ የተሻለ ፡ የግምት ፡ ስጠታ ፡ ስላለው ፡ ነገሮቱ ፡ ከሚናገረው ፡ የሚበዛው ፡ ስለሚያዝለት ፡ ነው ። ጥሩ ፡ ኒጋዴ ፡ የሚባለውም ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚወደደውን ፡

ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚገዛ ፡ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ የሚረክሰውን ፡ ገምቶ ፡ ዛሬ ፡ የሚሸጥ ፡ ነው ። ታዲያ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግምት ፡ የገብያውም ፡ የሰውም ፡ ሁኔታ ፡ ተጠንቶ ፡ የሚደረስበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲሁ ፡ የሚገኝ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ የገብያና ፡ ያጋለሰ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሰው ፡ ሁኔታ ፡ ጭምር ፡ መገመት ፡ የምችል ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ነኝ ፡ ማለቴ ፡ ነው ።'' አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ ትንሽ ፡ ፍርጥም ፡ ብለው ።

''ይህ ፡ ሁሉ ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ እስዎ ፡ እንዳሉት ፡ ጥሩ ፡ ጠንቁዋይም ፡ ይሁን ፡ ጥሩ ፡ ነጋዴ ፡ ከሚገምቱት ፡ አብዛኛው ፡ እንጂ ፡ ሁሉ ፡ ስለማይዝ ፡ ስለኔ ፡ የገመቱት ፡ ከማይዘው ፡ ከጥቂቱ ፡ መሀከል ፡ ሊሆን ፡ እያችልም?''

''ይሁን ፡ ተለስኝ ፡ ይሆናል !'' አሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በዛብህ ፡ ምስጢሩን ፡ ሊነግራቸው ፡ አለመፍቀዱን ፡ ሲያዩ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፋ ፡ አደረጉና ።

''አገርህም ፡ ይሁን ፡ እዚህ ፡ የተቸገርህበት ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ልረዳህ ፡ እችል ፡ እንደሆነ ፡ ብዬኮ ፡ ነው ፡''አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ነጋድራስ ።

''እስከ ፡ ዛሬ ፡ የረዱኝ ፡ መቸ ፡ አነሰና?''

''እየ ----እባክህ ፡ እስከ ፡ ዛሬስ ፡ ምንም ፡ አላደረግሁልህ ፡ ልቤ ፡ ወደ ፡ ገብያው ፡ ተሰቅሎ ። አሁን ፡ መሄጃየ ፡ ስለደረሰ ፡ እንድ ፡ ቦታ ፡ ስትይዝ ፡ አይቼህ ፡ እንድሄድ ፡ ነበር ። እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሩፋኤል ፡ ትሄዳለህ! እዚያ ፡ ካህናቱ ፡ እጅግም ፡ ስለማይጠጉት ፡ ነፍት ፡ ቦታ ፡ አይጠፋም ፡ ይባላል ።''

''ከማህሌት ፡ ተለይቼ ፡ አላውቅም ።''

''ካለቃው ፡ ተዋውቀህል ?''

''የለም ። እሳቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይመጡም ፡ ሲመጡም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ስለሚከባቸው ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ ሊያገኛቸው ፡ የሚችል ፡ አይመስለኝም ።''

''ቆይ ፡ ነገ ፡ ጥዋት ፡ ገበያ ፡ መሄዱን ፡ ትቸ ፡ እደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዘንድ ፡ እወስድህና ፡ እሱ ፡ ያገናኝህል ።''

''ማነው ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ?''

''የኛ ፡ ነው ፡ ያገራችን ፡ የሞጣ ፡ ሰው ፡ ነው ። በቀደምም ፡

እስቢው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ለመሄድ ፡ ስቸኩል ፡ ረሳሁት ።''

በበነጋው ፡ እሁድ ፡ ጥዋት ፡ ነጋድራስ ፡ ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ግር ፡ የሸጡበትን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ሀሚድ ፡ የሱፍ ፡ ከሚባል ፡ ቱጃር ፡ ጋር ፡ ቀጠሮ ፡ ቢኖራቸው ፡ ወደሱ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ እሳቸው ፡ በዛብህን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄዱ ።

ሩፋኤል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዳሴ ፡ ውጭ ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎቱ ፡ አልቆ ፡ ካህናቱ ፡ ለግብር ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ ሊሄዱ ፡ ሲጠራሩ ፡ ደረሱ ። ደብተራ ፡ መንበሩንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ አገኙትና ፡ ከበዛብህ ፡ ጋር ፡ አስተዋውቀው ፡ ብርቱ ፡ ስራቸውን ፡ ትተው ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ የሄዱበትን ፡ ጉዳይ ፡ እንድ ባንድ ፡ ዘርዝረው ፡ ነገሩት ።

''ከዛራስ ፡ ከነገ ፡ ማለፍ ፡ የለበትም ፡ ማለትዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያስቸገረኝ ፡ ጊዜ ፡ ከሰጡኝ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ጋር ፡ ማስተዋወቁም ፡ ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ማስታወሱም ፡ አያስቸግረኝምኮ ፡ ነጋድራስ ! እለቃ ፡ ዛሬ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እግቢ ፡ ግብር ፡ ስለሚውሉ ፡ ነገ ፡ ጥዋትም ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ ይሄዳሉ ፡ ተብሎ ፡ ስለሚወራ ፡ ሳይመች ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ቃል ፡ አባይ ፡ አድርገው ፡ እንዳይጣሉኝ ፡ ፈርቼም ፡ ነው ። መቸም ፡ እስዎ ፡ ስራዎም ፡ ሆነ ፡ ቃልዎ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚዛን ፡ ነው !'' አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ፍርጥም፡ ብሎ ።

''አደለምኮ ፡ መንበሬ ፡ ግቢ ፡ ቢውሉ ፡ ግቢ ፡ ያድራሉ ? ግታም ፡ ቢሆን ፡ እቤታቸው ፡ ድረስ ፡ ወስደህ ፡ እገናኝተህ ፡ ስራ፡ እንዲሰጡት ፡ አደራ ፡ በላቸው ። በፈለግህበት ፡ ጊዜ ፡ እቤታቸው ፡ የምትገባ ፡ ባለሙዋል ፡ መሆንህንና ፡ እንተ ፡ ካልሀቸው ፡ የማይወጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ሰምቻለሁ ። እንግዲህ ፡ አደራ ፡ ለእሱ ፡ የምታደርገውን ፡ ሁሉ ፡ ለኔ ፡ እንደምታደርገው ፡ ቁጠረው !'' ሲሉ ፡ ነጋድራስ ፡ በደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ላይ ፡ እንድ ፡ አይነት ፡ ስልጣን ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ ባለብርቱ ፡ ውለታው ፡ መሆናቸው ፡ ለበዛብህ ፡ ተሰግውና ፡ ጉዳዩ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቁና ፡ መንገድ ፡ የያዘለት ፡ መስሎ ፡ ታያቸው ፡ ደስ ፡ አለው ።

'' እየ --- ብርቱ ፡ ሽክም ፡ ጣሉብኝ ፡ ነጋድራስ ፡'' አለ ፡

ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ እውነትም ፡ የጣሉበት ፡ ሽክም ፡ እንደ ፡ ከበ ደው ፡ ሁሉ ፡ ትከሻውን ፡ ትንሽ ፡ ሳበጥ ፡ አንገቱን ፡ ወደታች ፡ ሰበር ፡ አድርጎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዬ ።

ከዚያ ፡ ነጋድራስ ፡ ከሁለቱ ፡ ደብተሮች ፡ ተለይተው ፡ ወደ ሰራቸው ፡ ሲሄዱ ፡ " አንድ ፡ ነገር ፡ አሰብሁ ፡" አለ ፡ ደብተራ መንበሩ ።

" ምን ?"

"ማታ ፡ እቤታቸው ፡ ሄደን ፡ ከምናስቸግራቸው ፡ ለምን ፡ አሁን ፡ እግሲ ፡ አንሄድ ? እዚያ ፡ ከግብር ፡ ሲወጡ ፡ እናገኛቸዋለን ፡ ወዲያውም ፡ ግብር ፡ እንበላለን ።"

" ማን ፡ ያስገባናል ?"

"መቸስ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ተጠርቶ ፡ ሄዶ ፡ የሚበላ ፡ የለ ፡ ያው ፡ እግሩ ፡ ያደረሰውና ፡ እዚያ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ የሚበላው ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚገባ ፡ እንገባለን ።"

ደብተራ ፡ መንበሩና ፡ በሳብሀ ፡ ወደ ፡ ግሲ ፡ ሲሄዱ ፡ ገና ፡ ከሩቅ ፡ ነጋሪት ፡ እያስተጋባ ፡ "ገብር ፤ እር-እር-ገብር" ሲል ፡ በሳ ብሀ ፡ ሰማና ፡ " የምን ፡ ነጋሪት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የምንሰማው ?" አለ ።

" ሰውን ፡ ለግብር ፡ የሚጠራ ፡ ነው ።"

" ሁልጊዜም ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ የሚበላ ፡ እንዲህ ፡ በነጋሪት እየተጠራ ፡ ነው ?"

"አዳ ፡ ግብር ፡ ሲሆን ፡ አዎ ። ከዛሬ ፡ ቀደም ፡ አይተህ ፡ አታ ውቅም ?"

"የለም ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ።"

"ማየቱ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ መብላቱን ፡ ግን ፡ እኔ ፡ አልወደውም፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ዛሬ ፡ እንኩዋ ፡ ካህኑ ፡ ሁሉ ፡ ሲሄድ ፡ እኔ ፡ ተለ ይቼ ፡ ቀርቼ ፡ የነበረ ። ታዲያ ፡ እየውልህ ፤ በኔ ፡ ጉሮሮ ፡ ውረድ ፡ ያለው ፡ እህል ፡ ውሀ ፡ የማይቀር ፡ ሆኖ ፡ ነጋድራስን ፡ ምክናያት፡ አድርጎ ፡ አመጣኝ ። ነጋድራስ ፡ ባለብርቱ ፡ ውለታየ ፡ ናቸው ። ካገሬ ፡ አምጥተው ፤ ስራ ፡ እስካገኝ ፡ ሰንቅ ፡ ሰጥተው ፡ እዚህ ፡ ያደረሱኝ ፡ እሳቸው ፡ ናቸው ። ታዲያ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ አድርጌላ ቸው ፡ አላውቅም ፤ ሲመጡ ፡ እንኩዋ ፡ ጠይቂያቸው ፡ አላውቅም።"

" በጣም ፡ ጥሩ ፡ ሰው ፡ ናቸው ።" አለ ፡ በሳብሀ ።

እግሲ ፡ ሲደርሱ ፡ ከመጀመሪያው ፡ አጥር ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ በቅሎና ፡ በቅሎ ፡ ያዝ ፡ አሽከር ፡ ሞልቶታል ። ከመጀመሪያው ፡ አጥር ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ ያለውን ፡ ሰፈ ፡ ሜዳ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሞልቶታል ። ከዚያ ፡ እግብር ፡ መብያው ፡ አዳራሽ ፡ ድረስ ፡ አለፍ ፡ አለፍ ፡ እያለ ፡ ብዙ ፡ አቁዋራጭ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። በያቁዋራጩ ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ሜዳ ፡ ሁሉ ፡ እታች ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ መላወሻ ፡ የሌለበት ፤ ሰው ፡ ብቻ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ የሞላው ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሳያቁዋርጥ ፡ የሚነርፈው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እዬመጣ ፡ በላይ ፡ በላይ ፡ ሲጨመር ፡ ያ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ የሞላ ፡ የሚመስለው ፡ ግሲ ፡ ሁሉንም ፡ እዬ ተቀበለ ፡ ይውጣል ።

እንዳንዶቹ ፡ መኩዋንንት ፡ ታጅበው ፡ መጥተው ፡ ገና ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ ሳይገቡ ፡ ከበቅሎ ፡ ይወርዱና ፡ እዚያው ፡ ውጭ ፡ አደግድገው ፤ እጀባቸውን ፡ ትተው ፤ የሁለተኛውን ፡ በር ፡ ገብተው ፡ እዚያ ፡ ያርፋሉ ። አንዳንዶቹ ፡ በበቅሎ ፡ እንዳሉ ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ ገብተው ፡ እዚያ ፡ ደመር ዱና ፡ አደግድገው ፡ የሶስተኛውን ፡ በር ፡ ሲገቡ ፡ ይታያሉ ። እንዲሁም ፡ እን ደዬማእርጋቸው ፡ ከሶስተኛው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አቁ ዋራጭ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በዘቅሎ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሲገቡ ፡ የሚ ታዩ ፡ ነበሩ ። ሰም ፡ የለሹ ፡ ተራው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንኩዋን ፡ በበ ቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ በግሩም ፡ ቆሞ ፡ ሁለተኛውን ፡ በር ፡ መግባት ፡ አይችልም ።

ያ ፡ ሁሉ ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሲገመት ፡ የማችል ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ህዝብ ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እዬገባ ፤ ከዚያ ፡ እስካዳራሹ ፡ ባሉት ፡ ብዙ ፡ ጠባብ ፡ በሮች ፡ እዬተጣፉ ፡ በዬማእርጉ ፡ ሲተመጥ ፡ ካረፈደ ፡ በሁዋላ ፡ ከሁለ ተኛው ፡ ጀምሮ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ተዘጉና ፡ እላይ ፤ አዳራሹ ፡ አጠገብ ፡ ከተቀመጡት ፡ መኩዋንንት ፡ ጀምሮ ፡ ለግብር ፡ መከልከል ፡ ተጀመረ ።

በሳብሀ ፡ የህዝቡን ፡ ብዛት ፡ ሲያይ ፡ እዚያ ፡ እሱ ፡ በነበረበት ፡ ለሰፈረው ፡ ተራ ፡ ህዝብ ፡ ያነሰት ፡ ፈንታ ፡ ይደ

ርሰዋል ፡ ብሎ ፡ አልገመተም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ባዳራሹ ፡ አጠገብና ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውጪ ፡ በነበረው ፡ ሜዳ ፡ የተቀመጠው ፡ መኮዋንን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እዬተኮለኮለ ፡ በጸጥታና ፡ መልክ ፡ ባለው ፡ አሠዩዋን ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ ሌላው ፡ ከዚህ ፡ መሰሰ ፡ እዬተባለ ፡ በጅምላ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ መንጋ ፡ እዬተነዳ ፡ መግባት ፡ ስለ ጀመረ ፡ ከሁለት ፡ ሰአት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እላይ ፡ ግብሩ ፡ ከሚበላበት ፡ አዳራሽ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ድረስ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ብሎ ፡ ሞልቶ ፡ ምን ፡ ቦታ ፡ ይበቃው ፡ ይሆን ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገብቶ ፡ አልቆ ፡ በዛብህ ፡ የነበረበት ፡ የተራው ፡ ሀዝብ ፡ ፈንታ ፡ ደረሰ ። ብቻ ፡ ያገባቡ ፡ ስነ ፡ ስራት ፡ እንደ ፡ በዛብህ ፡ ለመ ጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለሚያየው ፡ ሰው ፡ ከማስገረሙም ፡ ሌላ ፡ እጅግ ፡ የሚያሰቅቅ ፡ ነበረ ።

ከላይ ፡ ካደራሹ ፡ አጠገብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጀመሪ ያው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በያቁዋራጩ ፡ በረኛ ፡ ባካባቢው ፡ የነበ ረው ፡ የከልካይ ፡ ብዛት ፡ ቁጥሩ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማ ለት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ አጋፋሪ ፡ የያዘው ፡ ረጉኝም ፡ ጨፈቃ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ቢሰበሰብ ፡ አንድ ፡ አዳ ራሽ ፡ ይሰራል ።

የበላይ ፡ አጋፋሪዎች ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ አይተው ፡ ሰው ፡ በርከት ፡ ብሎ ፡ እንዲገባ ፡ ሲያዝዙ ፡ ሰው ፡ በሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ አጋፋሪ ፡ ከዚህ ፡ መለስ ፡ ተነሱ ፡ ይልና ፡ በመንጋ ፡ ያገዛል ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተነ ስቶ ፡ እዬተራበሸ ፡ አቅም ፡ የሌለው ፡ ሲወድቅ ፡ አቅም ፡ ያለው ፡ በላዩ ፡ እዬቆመ ፡ አጋፋሪዎች ፡ ሲደበድቡት ፡ ጨፈ ቃቸው ፡ በላዩ ፡ እየተሰባበረ ፡ በሩን ፡ ለመግባት ፡ ሲሮጥ ፡ ከሞት ፡ የሚሸሽ ፡ እንጂ ፡ መብል ፡ የሚፈልግ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ እዬተራበሸ ፡ ሁሉም ፡ አይኑን ፡ እዬጨፈነ ፡ የሚቆምበትን ፡ ሳያውቅ ፡ እጁን ፡ የገፋ ፡ አካሉ ፡ ክፍል ፡ እን ዳልሆነ ፡ ሁሉ ፡ በላዩ ፡ ለሚወርድበት ፡ የጨፈቃ ፡ መአት ፡ እዬጋረደ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አጋፋሪዎችንም ፡ አሸንፎ ፡ እንደ ፡

ውሀ ፡ ሙላት ፡ ጠርጎ ፡ ይዘዋቸው ፡ ይገባል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከታች ፡ አመጣጡን ፡ ያዩና ፡ አጋፋሪዎች ፡ ቶሎ ፡ ተረዳድተው ፡ በሩን ፡ ዘግተው ፡ በጨፈቃ ፡ ደብድበው ፡ ይመልሱታል ።

ከሁለተኛው ፡ አቁዋራጭ ፡ ውስጥ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ እዬተነዳ ፡ እዬተነሳ ፡ ሆራ ፡ እንደሸተተው ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ አፍንጫውን ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲንጋጋ ፡ በግድ ፡ እዬተደበደበ ፡ እዬተመሰሰ ፡ ከወዲህ ፡ ወዲያ ፡ ከወ ዲያ ፡ ወዲህ ፡ ሲታመስ ፡ ቆይቶ ፡ ገብቶ ፡ ሲያልቅ ፡ በዛብህ ፡ በነበረበት ፡ ሜዳ ፡ የነበረው ፡ ሀዝብ ፡ መግባት ፡ ጀመረ ።

እዚያ ፡ የነበረው ፡ ሀዝብ ፡ የመጨረሻው ፡ ስም ፡ የለሹ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ዱላው ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስመርጥ ፡ ነበር ። በዛብህ ፡ ገና ፡ እጅግመሩን ፡ ሲያይ ፡ እዚያ ፡ ረብሻ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ በጨናው ፡ ለመውጣት ፡ የማይችል ፡ ስለ ፡ መሰሰው ፡ ግብር ፡ ለመግባት ፡ ጭራሽ ፡ አለመሞከርን ፡ መረ ጠና ፡ በሩቁ ፡ አጥሩ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ ሰቀላ ፡ ቤት ፡ ስላዬ ፡ ወደ ዚያ ፡ ሸሸ ።

እሰቀላው ፡ ጥግ ፡ ሁለት ፡ ጭዋ ፡ ሰዎች ፡ እዘን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ ሁሉ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቁጭ ፡ ብለው ፡ ነበር ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ይነጋገራሉ ።

በዛብህ ፡ ግብር ፡ መብላቱም ፡ ቢቀርበት ፡ ለመብላት ፡ የሚፈልጉት ፡ የሚያደርጉትን ፡ ተጋድሎና ፡ ያን ፡ የሚያስገ ርም ፡ ረብሻ ፡ ማየቱ ፡ እንዳይቀርበት ፡ ከሩቅ ፡ የሚመለከትበት ፡ ቦታ ፡ ሲፈልግ ፡ አሁሉቱ ፡ ሰዎች ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ቁዋጥኝ ፡ ደንጋይ ፡ ስላዬ ፡ እዚያ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ ረብሻው ፡ ያስነሳው ፡ አጉዋራ ፡ ግቢውንና ፡ ከግቢውም ፡ በላይ ፡ ጠፈሩን ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ክባድ ፡ ጭጋግ ፡ ሸፍኖት ፡ ስለነበረ ፡ እዚያ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግልና ፡ ድብልቅልቅ ፡ የሚነሳ ውን ፡ አጉዋራ ፡ አይቶ ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ ማየት ፡ አይቻ ልም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ አጉዋራውን ፡ ብቻ ፡ እያዬ ፡ አጉዋራው ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ትግል ፡ እዬገመተ ፡ ተቀ መጠ ።

“ ላጋፋሪ ፡ ተምትሚ ፡ ጉበ ፡ ሳልሰጥ ፡ አረተኩ ፡ ነው --- የሞስብ ፡ ጉዋደኞቸ ፡አመሁዋንንት ፡ ማረፊያ ፡ ሲአመጡ - - - እኔን ፡ ከነሱ ፡ ለይቶ ፡ እዚህ ፡ ተአምጠህ ፡ ጠብእ ፡ እነሱ ፡ ሲገቡ ፡ ትሰራለህ ፡ ያለኝ ። እየው ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ እዚህ ፡ ተአምጠን ፡ ተራውን ፡ ሰው ፡ መደዴውን ፡ ማስገባት ፡ ጀመሩ ።” አሉ ፡ አዝነው ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ እንባቸው ፡ ባይናቸው ፡ ቅርሮ ፡ ብሎ ፡ እዬታዩ ።

“ እኔሰ ፡ ያው ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ አይደል ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ጥፋት ፡ ተገኝብኝ ! ከሙር ፡ ሜዳ ፡ ስሸሽ ፡ ታዬሁ ? ወይሰ ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ አልፈጽም ፡ አልሁ ? እንደ ፡ ግዞተኛ ፡ ከጉዋደኞቸ ፡ ተሰይቼ ፡ ከገዛ ፡ አሽከሮቼ ፡ በሁዋላ ፡ እንድቀር ፡ መደረጉ ፡ ጉቦ ፡ ባለመስጠቴ ፡ ነው ! ” አሉ ፡ ሁለተኛው ።

“ የንጉስ ፡ ግብርና ፡ አርባን ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፡ ከረድኤቱ ፡ ለመሀፈልና ፡ ጌታችን ፡ ከተራ ፡ ህዝብ ፡ እንድንሰይበት ፡ የሰጡንን ፡ ደረጃ ፡ ለመጠበእ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንጀራማ ፡ በዬ ቤታችን ፡ ከኛ ፡ ተርፎ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እናበላ ፡ የለ ? ” አሉ ፡ አይናቸውን ፡ እንባ ፡ የሞላው ፡ ሰው ።

ሁለቱ ፡ መኮዋንንት ፡ እንዲህ ፡ እያዘኑ ፡ ሲወያዩ ፡ ከከልካዮች ፡ አንዱ ፡ እዬሮጠ ፡ መጥቶ ፡ አይናቸው ፡ እንባ ፡ ያዘለውን ፡ መኮንን ፡ ጠራቸው ።

“ አሁን ፡ ከማን ፡ ጋር ፦ ልታስኸምጡኝ ፡ ነው ፡ የምትጠሩኝ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ? ካሽከሮች ፡ ጋር ፡ ልታስኸምጡኝ ፡ ነው ? ግዴለም ፡ ተውት ፡ እግዚአብሄር ፡ ይስጥልኝ ! ያደባባይ ፡ አምላክ ፡ ያፈራርደን ፡ ብቻ ! እንግዴህስ ፡ እቤቴ ፡ እሄዳለሁ !” አሉና ፡ ሰውዬው ፡ ለመሄድ ፡ ሲነሱ ፡-

“ ኢሂ ! ኢንጉሲን ፡ ጊብሪሞ ፡ መርጌጣትኖ ? ና ፡ ማሊስ ! ” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ በብርቱ ፡ ቁጣ ፡ የተሰባበረ ፡ ጩፈቃውን ፡ አስቀድሞ ።

አከርፈው ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሊሄዱ ፡ የተነሱት ፡ ሰውዬ ፡ ታማዶ ፡ የቆዬው ፡ ቁጣቸው ፡ ገንፍሎ ፡ ከልካዩን ፡ ለማንቅ ፡ እዬተንቀጠቀጡ ፡ እጃቸውን ፡ ከዘረጉ ፡ በሁዋላ ፡ የጌጉስ ፡ ግብር ፡ አልበላም ፡ ብለው ፡ ከከልካይ ፡ ጋር ፡ መጣላታቸው ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችለውን ፡ በመገመትም ፡ ይሁን ፡ በሌላ ፡ ቁጣቸውን ፡ እንደገና ፡ ውጠው ፡ በረድ ፡ ሲሉ ፡ ሲያይ ፡ ከልካዩ ፡ በበኩሉ ፡ በጣም ፡ ተቆጣ ።

“ኢንጉሲን ፡ ጊብሪ ፡ ኢናትን ፡ ኢንጀራኖ ፡ ፈሊጋለሽ ፡ በላል ፡ አልፈሊጋለሽ ፡ አልበላል ! አይ ፡ ኢናት ፡ አራዳን ፡ ጎርጊ.....ስ ! ኢስቲ ፡ ቂስቂስን ፡ ብላል ፡ ውርዳቲን ፡ መጣለሽ ! ሊቢን ፡ አርጋል ! ኢንጉሲን ፡ ጊብሪ ፡ ጊዲዳት ፡ ባላልናንጂ ፡ ውዲዳት ፡ ባላልኖ ? ጊ !” አለ ፡ አጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ እኒያን ፡ ሰውዬ ፡ በመናቅና ፡ በመጸየፍ ፡ ቁጣው ፡ እንደላት ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ሲነድ ፡ እዬታዩ ።

አጋፋሪ ፡ ጉደታና ፡ አከርፈው ፡ ለመሄድ ፡ የተነሱት ፡ ሰው ፡ ተፋጠው ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ እንደ ፡ ካለባበሳቸውና ፡ ካጀባቸው ፡ የከልካይ ፡ ብዛት ፡ በግምት ፡ ካጋፋሪዎች ፡ ሹማምንት አንዱ ፡ የሚመስሉ ፡ ሰው ፡ መጡና ፡ ሁለቱንም ፡ አዝነው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ሲያስጠሩዋቸው ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ አዘን ፡ ወዲያው ፡ ተረስቶ ፡ ሁለቱም ፡ ፈታቸው ፡ በቅጥበት ፡ በደስታ ፡ በርቶ ፡ ያጋፋሪዎችን ፡ ሹም ፡ ተከትለው ፡ ሄዱ ።

በዛብህ ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ መብላት ፡ ግዴታ ፡ እንጂ ፡ ውዴታ ፡ አለመሆኑን ፡ ካጋፋሪ ፡ ጉደታ ፡ ሲሰማ ፡ አጋፋሪው ፡ ካኮረፉት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እዬተጨቃጨቀ ፡ ልብ ፡ ሳያደርገው ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ደንጋይ ፡ ወረደና ፡ ሄዶ ፡ ግብር ፡ ለመብላት ፡ ከሚተራመሰው ፡ ህዝብ ፡ ጋር ፡ ተጨመረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሚበላው ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ የቀረው ፡ ጥቂት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ዱላውም ፡ ረብሻውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ተቀንሶ ፡ ብዙ ፡ ሳይንገላታና ፡ ዱላም ፡ ሳያገኘው ፡ ገባ ።

እንደ ፡ ገባ ፡ አብሮት ፡ የገባው ፡ ሁሉ ፡ ይህና ፡ ቦታ ፡ ፍለጋ ፡ እዬጣለው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲሮጥ ፡ እበሶ ፡ አጠገብ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ ስላገኘ ፡ ሳይገፋ ፡ ለመውጣትም ፡ እንዲመቸው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠና ፡ መብላቱን ፡ ጉዶ ፡ አዳራሹንና ፡ የግብሩን ፡ ስነ ፡ ስረት ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ።

ያዳራሹ ፡ መጠን ፡ በወረዱም ፡ ሆነ ፡ በቁመቱ ፡ እሱ ፡ ከተቀመጠበት ፡ ሆኖ ፡ ዳርቻውን ፡ አጣርቶ ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ።

ልክ ፡ በመግቢያው ፡ ዘር ፡ እንጣር ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ሲል ፡ ባንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ድልዳል ፡ ላይ ፡ ከፊት ፡ በኩል ፡ በሰፊው ፡ ግልጥ ፡ የሆነ ፡ ጠርዙ ፡ ሁሉ ፡ በወርቅ ፡ የተከፈፈና ፡ ራሱም ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ የሆነ ፡ ስፋቱ ፡ ካንድ ፡ መጠነኛ ፡ ቤት ፡ የማያንስ ፡ እጎዘር ፡ ይታያል ። እዚያ ፡ እጎዘር ፡ ውስጥ ፡ እንዲሁ ፡ በወርቅና ፡ የቀለሙ ፡ ዙዘር ፡ የዘርዝን ፡ አዳል ፡ ተከትሎ እዬተለዋወጠ ፡ እይን ፡ በሚያሳስት ፡ ዘር ፡ ያጌጠ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዙፋን ፡ ተዘርግቶ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የለበሰው ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ጸሀይ ፡ ጮራ ፡ እይን ፡ የሚለሜጥ ፡ ሰው ፡ ተቀምጦዋል ፡ ''እእ . . . ! እኒያ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ጃንሆይ ፡ ናቸው ፡ ''አለ ፡ በዛብህ። ከዙፋኑ ፡ አካባቢ ፡ እድልዳሉ ፡ ላይ፡የተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ጸያቂ ፡ ነፍሳት ፡ ከጌታቸው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አብረው ፡ የሚካፈሉ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ። ስጋውን ፡ ዘወሳሳ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ የሲጋ ፡ መልከኞች ፡ ቀሚስ ፡ አልብሰው ፡ እዬተሸከሙላቸው ፡ ጠጁ ፡ ባሳላፊዎች ፡ እጅ ፡ የበሰለ ፡ እንሁያ ፡ መስሎ ፡ ተንዠርጎ ፡ እዬቀረበላቸው ፡ ዘጸጥታ ፡ ሲበሉ ፡ ሲጠጡ ፡ በውነት ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ይመስላሉ ። ከዙፋኑ ፡ አቅራቢያ ፡ ድልዳሉን ፡ ከዘው ፡ የቆሙት ፡ አምዶች ፡ እንሁዋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለም ፡ ባለው ፡ ጨርቅ ፡ ተሸልመው ፡ ከሩቅ ፡ ሲታዩ ፡ ላይን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ያሰኛሉ ። ከዙፋኑ ፡ ራቅ ፡ ከድልዳሉ ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሲሄድ ፡ ግን ፡ የሁሉም ፡ እይነት ፡ ይለወጣል ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከድልዳሉ ፡ በታች ፡ እደራሽን ፡ በወርዱም ፡ በቁመቱም ፡ ከዳር ፡ እስከዳር ፡ የሞላው ፡ ህዝብ ፡ እንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ እየተደራረበ ፡ ለፍሮ ፡ የሚተራመስ ፡ የንብ ፡ ሰራዊት ፡ እንጂ ፡ በተራ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ እይመስልም ። ስጋውን ፡ መልከኞች ፡ ሙዳ ፡ ሙዳ ፡ አድርገው ፡ እዬቆራረጡ ፡ በሳጠራ ፡ ሞልተው ፡ እሽክመው ፡ ያመጡና ፡ ከሩቅ ፡ እየወረወሩ ፡ እንዱን ፡ ፊቱን ፡ ሌላውን ፡ ደረቱን ፡ ሲሉት ፡ ልበኛ ፡ ቀልቦ ፡ ያስቀረዋል ፡ የዘንጋ ፡ እምልጠት ፡ እመራት ፡ ይጠድቅበታል ። ጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ ጠላት ፡ እንደሚያሳድዳቸው ፡ እዬተጣደፉ ፡ ጠጁን ፡ በከባያ ፡ እዬቀዱ ፡ ሲያድሉ ፡ በሚጠጡት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡

እስኪደርስ ፡ ግማሹ ፡ ያክል ፡ በሰውነታቸውም ፡ በልብሳቸውም ፡ ይፈሳል ፡ ወዲያው ፡ የተረፈውን ፡ ቢጨርሱም ፡ ባይጨርሱም ፡ ላልደረሰው ፡ ለማድረስ ፡ ኩባያውን ፡ ከጃቸው ፡ ነጥቀው ፡ ይወስዱባቸዋል ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ የኩባያውና ፡ የቢላዋው ፡ ኩዋኩዋታ ፡ ያሳላፊውና ፡ ያቅራቢው ፡ ያጋፋሪው ፡ ጫጫታ ፡ በውነት ፡ ራስ ፡ ያሳምማል። አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ የቆሙትን ፡ ወጋግራዎች ፡ እዬተደገፉ ፡ የቆሙ ፡ ብዙ ፡ አዝማሪዎች፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ እጃቸው ፡ መሰንቆውን ፡ ሲገዘግዝ ፡ ያንገታቸውም ፡ የደም ፡ ስር ፡ ተገትሮ ፡ እፋቸው ፡ በሙሉና ፡ በከፊል ፡ ሲከፈት ፡ በማየት ፡ የሚያዘምሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ከመገመት ፡ በቀር ፡ የመሰንቆውም ፡ ሆነ ፡ የነሱ ፡ ድምጽ ፡ በጭራሽ ፡ አይሰማም ። እንዲሁም ፡ ጥሩምበኞች ፡ እምቢልተኞችና ፡ መለከተኞች ፡ እያደገደጉ ፡ ተደርድረው ፡ መሳሪያቸውን ፡ በያፋቸው ፡ ለግበው ፡ ጉንጫቸው ፡ እንደፊኛ ፡ ተነፍቶ ፡ እይናቸው ፡ ፈጦ ፡ የደም ፡ ስራቸው ፡ በዬግንባራቸው ፡ ተገትሮ ፡ ሲታዩ ፡ ሁሉም ፡ በዬመሳሪያቸው ፡ ሲጫወቱ ፡ ፎቶግራፍ ፡ የተነሱ ፡ ምስሎች ፡ እንጂ ፡ ያነሉት ፡ እዚያ ፡ ቆመው ፡ የሚነፉ ፡ ነፍስና ፡ ስጋ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እይመስሉም ።

በዛብህ ፡ ያነለት ፡ አቤተ ፡ መንግስቱ ፡ እደባባይ ፡ ከደረሰ ፡ ጀምሮ ፡ ሲያየው ፡ የዋለውና ፡ ያንጊዜም ፡ እዚያ ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚያየው ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ መንግስቱ ፡ ከነበረው ፡ አሳብና ፡ ግምት ፡ በጭራሽ ፡ የተለዬ ፡ ሆኖበት ፡ በመገረም ፡ ፊት ፡ ፍዝዝ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከት ፡ በጎኑ ፡ የተቀመጠው ፡ ሰው ፡ በከርን ፡ ጎሰም ፡ እደረገና ፡ ወደጀሮው ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ''ለማህ ? ወንድሜ ፡ እንግዲህስ ፡ ጠጅ ፡ ከታደለ ፡ ያስወጡናል! ስለዚህ ፡ መቸም ፡ ግብር ፡ በልቼ ፡ መጣሁ ፡ እንጂ ፡ እይቸ ፡ መጣሁ ፡ አይባልምና ይህን ፡ ለማለት ፡ እንዲመችህ ፡ ባይሆን ፡ ከስጋው ፡ ትንሽ ፡ ብላ ፡ '' አለው ።

''እእ ? እሺ ፡'' አለና ፡ በዛብህ ፡ እይኑን ፡ ወደንጀራው ፡ መለስ ፡ ቢያደርግ ፡ እንኩዋን ፡ ለመብላት ፡ ለማየቱም ፡ የሚያስፈራራ ፡ ሆነበት ። እንጀራው ፡ ከጥቁር ፡ ጭቃና ፡ ከሳር ፡ በስሉ ፡ ተጠፍጥፎ ፡ የደረቀ ፡ እንጂ ፡ ከህል ፡ የተጋገረ ፡ እን

ቀድሚ ፡ ገብቼ ፡ መውጣቱ ፡ ስለማይቀር ፡ መውጫውን ፡ ይገር ፡ እስከመጨረሻ ፡ ከጠበቅሁ ፡ አታመልጠኝም ፡ ብዬ ፡ ይሄው ፡ ቅድም ፡ የጠላሁ ፡ እጠብቅሀለሁ ። ''

''አለቃ ፡ ወጡ ? ''

''እሳቸውማ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ መጨረሻ ፡ ከሚወጡት ፡ መሀከል ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ መውጫቸው ፡ ነው ። ''

''እኔማ ፡ በገባንበት ፡ የምንጠላ ፡ መስሎኝ ፡ ተመለስ ፡ ሲባል ፡ ሳልሰማ ፡ ቶሎ ፡ ስመጣት ፡ ወደ ፡ ገባሁበት ፡ ዘዚ ፡ ስሮጥ ፡ አጋፋሪው ፡ እዬተመላለስህ ፡ ስትበላ ፡ ልትውል ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ብሎ ፡ መርመሮ ፡ ጣለኝና ፡ ይዩትልም ፡ ስወድቅ ፡ ፈራ ፡ ተጋጠ ። ''አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መሳቅ ፡ ብሎ ።

''አይ ---ጎደሎሀል ! አጋፋሪዎች ፡ ጨካኞች ፡ ስውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የማያዩ ፡ ናቸው ። ''

''እኔማ ፡ አዳራሹ ፡ በፈራ ፡ እዬዋጠ ፡ ዘሁዋላው ፡ የሚተፋ ፡ መሆኑን ፡ ሳላውቅና ፡ የሚገባ ፡ እንጂ ፡ የሚወጣ ፡ ሰው ፡ ስላላዬሁ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ እዬከተተ ፡ ገሃም ፡ የሚል ፡ ብዬ ፡ ገርሞኝ ፡ ነበር ። ''

በዛብህና ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ እመውጫው ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ቆመው ፡ ሲነጋገሩ ፡ የሩፋኤል ፡ አለቃ ፡ ብቅ ፡ ስላለ ፡ ሁለቱም ፡ ወደሳቸው ፡ ሄደው ፡ እጅ ፡ ነሱ ።

''አለ ---ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ምን ፡ ታያርጋላችሁ - እዚህ ፡ ፋሜችሁ ? ይህ ፡ በቀደም ፡ እጣነሞገር ፡ ሲመረ ፡ ያዬሁት ፡ ልጅ ፡ አያደለም ? ''አሉ ፡ አለቃው ፡ በዛብህን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ፡ እያዩ ።

''አዎን ፡ ነው ፡ ጌታየ ፡ አሱን ፡ ከገጠየ ፡ ጋር ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ገጠየን ፡ ነበር ፡ የምንጠብቀው ፡ ''አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

''ማለፊያ ፡ ማለፊያ ፡ ከየት ፡ መጣህ ? ''

''ከጎጃም ፡'' አለ ፡ በዛብህ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ ማፈር ፡ ብሎ ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡

ጀራ አይመስልም ። ወጡም ፡ እንዲሁ ፡ ወፈር ፡ ብሎ ፡ የተበጠበጠ ፡ ጭቃ ፡ ይመስላል ። ከዚያ ፡ እንጀራውን ፡ ተወና ፡ ከሰጋው ፡ ልብላ ፡ ልተው ፡ እያለ ፡ ሲያመነታ ፡

''ተነሱ ፡ በል ! ተመለሱ ፡ በል!'' አለ ፡ እዚያ ፡ አጠገብ ፡ ከቆሙት ፡ ያጋፋሪዎች ፡ ሹሞች ፡ አንዱ ። ከዚያ ፡ መጋፋቱ ማዳፋቱ ፡ ረብሻው ፡ ድብልቅልቁ ፡ እንደገና ፡ ተጀመረ ። በዛብህ ፡ አለዴቃው ፡ መጨረሻ ፡ አበሩ ፡ አጠገብ ፡ ስለነበረ ፡ የተቀመጠ ፡ ቶሎ ፡ ተነስቶ ፡ በገባበት ፡ በር ፡ ሲወጣ ፡ ሲሄድ ፡ አንዱ ፡ ከልካይ ፡ አንገቱን ፡ ይዞ ፡ ቢወረውረው ፡ ከመሬት ፡ ተደባለቀ ። ከዚያ ፡ ተነስቶ ፡ እንደገና ፡ ወደበሩ ፡ ለመሄድ ፡ ሲሞክር ፡ ''ወየታባቱ ፡ ሲሄድ ፡ ነው ? በል ! እዬተመላለሰ ፡ ሲበላ ፡ ሲውል ፡ አሰቦዋል?'' አለ ፡ ከልካዩ ፡ ስመማታት ፡ ዱላውን ፡ እያመቻቸ ። በዛብህ ፡ ግራ ፡ ገባውና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚወጣበት ፡ ሌላ ፡ በር ፡ መሆኑን ፡ ስላዬ ፡ ቶሎ ፡ ወደዚያ ፡ ሮጦ ፡ አመለጠ ። ከዚያ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩን ፡ አበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ሲጠብቀው ፡ አገኘ ።

''የት ፡ ጠፋኸኝ ? '' አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

''እስም ፡ ጠፋኝ ፡ እንጂ ! ጭራሽ ፡ አላገኝህም ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጬ ፡ ነበር ።''

''ወዲያው ፡ የመጀመሪያውን ፡ በር ፡ እንደገባን ፡ ካንድ ፡ አጋፋሪ ፡ ጋር ፡ ስነጋገር ፡ ባጠገቤ ፡ አልነበርህም ?''

''ያንጊዜማ ፡ አብሬም ፡ ነበርሁ ፡ የህዝቡ ፡ ብዛት ፡ አስገርሞኝ ፡ ስዚህ ፡ ሁሉ ፡ ህዝብ ፡ የሚሰላ ፡ ነገርስ ፡ ቢገኝ ፡ የሚሰላበት ፡ ቦታ ፡ ይገኛል ፡ ወይ ፡ እያልሁ ፡ በማያገባኝ ፡ ጉዳይ ፡ ገብቼ ፡ ይህን ፡ ሳወጣ ፡ ሳወርድ ፡ ቆይቼ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ አጣሁም ።''

''እኔማ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ የማውቀው ፡ አጋፊሪ ፡ ስላገኘሁ ፡ ላንተም ፡ ስኔም ፡ የተሻለ ፡ ቦታ ፡ እንዲሰጠን ፡ ትንሽ ፡ አጎረስሁትና ፡ እዬመራ ፡ የሁለተኛውን ፡ አቁዋራጭ ፡ በር ፡ አስገብቶ ፡ እዚያ ፡ የምቆይበት ፡ ቦታ ፡ ሲሰጠኝ ፡ ተከትለኸኛል ፡ መስሎኝ ፡ ዘወር ፡ ብል ፡ ስለጠፋህብኝ ፡ መቸም ፡ ካንተ ፡

“ድንት ፡ ድንት ፡ ሩፋኤል ፡ ማነልነል ፡ ትሻለህ ? ”

“ቦታ ፡ ቢገኝልኝማ —ለሱ ፡ ደጅ ፡ ለመጥናት ፡ ነበር ። ”

“እይነቱኛ ፡ ሙያህ ፡ ምንድነው ?”

“ለዚማና ፡ ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ተመርቄያለሁ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ሳለሁ ፡ መጽሀፍም ፡ አስተጥል ፡ ነበር ። ”

“እንዲያው ፡ ድምጻ ፡ መልካም ፡ ብቻ ፡ እያደለህም ፡ ባለሙያም ፡ ነህና ! ”አሉ ፡ አለቃ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መላቅ ፡ ብለው ።

“ነገ ፡ እቤት ፡ ድረስ ፡ ይዘኸው ፡ ና ፡ ”አሉ ፡ ቀጠሉና ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ዘወር ፡ ብለው ።

ከዚያ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩና ፡ በዛብህ ፡ አለቃን ፡ በቅሎ ዋቸውና ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ባሉበት ፡ እድርሰዋቸው ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡-

“እንኩዋን ፡ ደኅለህ ! እንግዴህ ፡ ምንድነው ፡ የደስደስ ፡ የምትሰጠኝ ? ”አለ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ።

“ስለምኑ ? ”አለ ፡ በዛብህ ።

“ስራ ፡ ስላገኘህ ፡ ”

“ገና ፡ መች ፡ አገኘው ? ”

“አለቃ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ከተናገሩ ፡ ስራ ፡ ሰጡህ ፡ ማለት ፡ ነው ። እኛ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ ደብተሮች ፡ እዱለቀቁ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስለሄዱ ፡ አንዳንድ ፡ ክፍት ፡ ቦታ ፡ አለ ፡ የቅኔ ፡ መምህራችንም ፡ በቅርቡ ፡ ሞተው ፡ ቦታቸው ክፍት ፡ ነው ። ልጅ ፡ ነህ ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እሱንማ ፡ ቢሰጡህ ፡ ጌትነት ፡ ነበር ። ”

“ያመወዙ ፡ ምን ፡ ያክል ፡ ነው ? ”

“ባሙት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንድ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለ ፡ ለም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ አለው ። ”

“እንግዲህ ፡ እሰም ፡ ይረዱኝ ፡ እኾይሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ግን ፡ ዘመድ ፡ አለኝ ? ስለሙያየ ፡ ልብምን ፡ ሞልተው ፡ ቢናገሩ ፡ የማሳፍረዎ ፡ አይደለሁም ። ለቅኔ ፡ መምህርነት ፡ መመረቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዲግ ፡ አለቃ ፡ ከነፉ ፡ ዘንደ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ መምህራን ፡ ወንበር ፡ ተሰጥቶኝ ፡ ብዙ ፡ ተግሪ ፡ አስተምር ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ታሪክ ፡ ይሁን ፡ ሰምና ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ሀብር ፡ ቅኔ ፡ ከጉባኤ ፡ ታና ፡ እስከ ፡ መወድስ ፡ አሰከ ፡ እጣነሞገር ፡ አፈታቸው ፡ ዘርፌ ፡ ላሳይ ፡ እችላለሁ ። ”

“ትልቅ ፡ እድል ፡ ነው ! ትልቅ ፡ እድል ! በል ፡ አሰቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ ፡ እንኩዋን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሙያ ፡ እያለህ ፡ ባያናርህም ፡ ለንጋድራስ ፡ ሁንኛው ፡ ስል ፡ የምችለውን ፡ ያክል ፡ ብያክም ፡ ይሰታኖ ፡ ነው ። መቸም ፡ ቀድሞ ፡ እንዳልሁህ ፡ አለቃ ፡ ስራ ፡ ሰጥተው ፡ ሩፋኤል ፡ እንደ-ትሆንላቸው ፡ መፈለጋቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ ፡ ብቻ ፡ ላረጋግጥልህ ፡ የግልችልና ፡ እግዚአብሄር ፡ እንዲረዳን ፡ መለመን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ እንዲሰጡህ ፡ ነው ። ብችል ፡ አሰቲ ፡ ግቶ ፡ ሄጀ ፡ እምክራለሁ ። ”

በዛብህ ፡ ያን ፡ ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ አልተኛም ። የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ቦታ ፡ አግኝቶ ፡ ጥሩ ፡ ቤት ፡ ተከራይቶ ፡ ሰልጡን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አሽከሮች ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሣ ፡ ሰርቆ ፡ አምጥቶለት ፡ ምሽቱ ፡ ሆና ! ግንንም ፡ ሳይረሩና ፡ ከግንም ፡ ሳይሸሽ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ” ሊቅ ፡ ባልና ፡ ምሽት ፡ ” እያለ ፡ እዱተገረመባቸው ፡ የሚኖሩት ፡ የደስታና ፡ የሩቅር ፡ ኑሮ ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ይታዱውና ፡ ወዲያው ፡ ደህ ፡ ምኞት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ሁሉ ፡ ልቡን ፡ የደስታ ፡ ሙቀት ፡ ሲያግለው ፡ ይሰማዋል ። ከዚያ ፡ ትንሽ ፡ ይቆይና ፡ “አለቃ ፡ አንቢ ፡ ይሉ ፡ ይሆን ? የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ ባይሰጡኝ ፡ ሌላ ፡ ሰራ ፡ እንደማላጣ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ አረጋግጦ ልኛል ። ለመሆኑ ፡ ከኔ ፡ የተሻለ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያገኛሉ ? አሰቲ ፡ ለሁሉም ፡ እግዚአብሄር ፡ ይርዳ !” ይላል ። ከዚያ ፡ ቀን ፡ እግቢ ፡ ሄዶ ፡ ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ ይታየዋል ። ህዝቡ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከላይ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ በዱላ ፡ እዱተደበደበ ፡ ሲንዳ ፡ እንዲያ ፡ እዱተደበደበ ፡ ከገባ ፡ በሁዋላ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ እጀንሆዩ ፡ ፈት ፡ እንዲበላ ፡ ተሰናድቶ ፡ የቀረበለት ፡ የእንጀራውና ፡ የወጡ ፡ አይነት ፡ አጋፋሪዎችና ፡ አሳላፊዎች ፡ የሚያስተናግዱበት ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ታዱው ።” የንጉስ ፡

ግብር ፡ ማለት ፡ ለ፟ነሰ ፡ እንዲሠ ፡ ያሰ ፡ ነው ! ” አለ ፡ቀን ፡ ሲያየው ፡ የዋለው ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ባይነ ፡ ህሊናው ፡ ፊት ፡ ተራ ፡ ገብቶ ፡ ሲሄድ ፡ እዩ፡ተመለከተ ፡ “ እረ ፡ ለመሆኑ ! ሙሉ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እዬገዙ ፡ ከዚያ ፡ የተሻለ ፡ እንጀራ፟ ፡ ወጥ ፡ አጥተው ፡ ነው ፡ ሰውን ፡ በነጋሪት ፡ ጠርተው ፡ እንዲያ ፡ ያሰ ፡ ነገር ፡ አቅርበው ፡ ብሉ ፡ የሚሉ ? ወይ፟ስ ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ባይቆጥሩት ፡ ይሆን ? ሰውስ ፡ ያን ፡ ለማየት ፡ እንኮዋ ፡ የሚያስፈራራ ፡ ነገር ፡ ለመብላት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ የሚሰ፡ዘ ገብበት ፡ ምን ፡ ይሆን ?” የንጉስ ፡ ግብር ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንጀራ፟ ፡ እቤታችን ፡ መች ፡ አጣን ? ” አሉ ፡ ከከል ካዩ ፡ ጋር ፡ የተጣሉት ፡ መኮንን ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ዛሬ ፡ እንዳዬሁት ፡ ከሆነ ፡ ሜሪ፟ሽ ፡ እያስመኘም ! ከድህ ፡ ቤት ፡ ተለምኖ ፡ የሚበላው ፡ ቁራ፟ሽ ፡ በስንት ፡ ጣሙ ! የሰ፟ም ፡ የንጉስ ፡ ግብር ፡ ለመብሉ ፡ አይደለም ፡ የሚፈለገው ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ይኖረ ዋል ! ምን ፡ ይሆን ? የንጉስ ፡ ግብር ! ግብር ፡ መች ፡ እዳ ፡ ነው። ታዲያ ፡ ንጉስ ፡ እዳ ፡ ይከፍላል ? የሰ፟ም ፡ ህዝብ ፡ ነው ፡ ለንጉስ ፡ እዳ ፡ የሚከፍል ። ነገር ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አልተስማማም ። ህ ዝቡ ፡ በላ ፡ እንጂ ፡ ምን ፡ እዳ ፡ ከፈለ ? አለ - - - -? አሁን ፡ አገኘ ሁት ! ህዝብ ፡ ለንጉስ ፡ የሚከፍለው ፡ የክብር ፡ እዳ ፡ ነው ! ህዝብ፡ ከሰውነት ፡ ወደ ፡ እንስሳነት ፡ ደረጀ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ተገ ፍቶ ፡ ተመትቶ ፡ የሰውነት ፡ መብቱንና ፡ ክብሩን ፡ ሁሉ ፡ ትቶ ፡ የማይበላ ፡ ነገር ፡ በልቶ ፡ ተንቆ ፡ ተደቅድቆ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገዛ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይበትና ፡ ንጉሱም ፡ ያን ፡ እያዩ ፡ ደስ ፡ የሚሰኙ በት ፡ ዘዴ ፡ ነው ! ከህብቱ ፡ ሀብት ፡ ከፍሎ ፡ እንደሚገብር ፡ ከሰ ውነቱ ፡ ከፍሎ ፡ ለንጉስ ፡ የሚገብረው ፡ የመንፈስ ፡ ግብር ፡ ነው ! ልክ ፡ መሰረቱ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ማስረጃውም ፡ ከንጉስና፡ ከትልልቅ ፡ መኮዋንንት ፡ ቤት ፡ በቀር ፡ በተራ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ግብር ፡ የሚባል ፡ ነገር ፡ የሰ፟ም ። ብዙ ፡ ሰው ፡ ተጠርቶ ፡ የሚበ ሳው ፡ ድግስ ፡ ባዘቦት ፡ የሚበ፟ሳው ፡ ራትና ፡ ምሳ ፡ ነው ፡ የሚበ ሳው ። ብቻ ፡ ሰው ፡ መሰረቱን ፡ ሳያውቅ ፡ በረኸም ፡ ጊዜ ፡ ልማ ድ ፡ የውርደቱን ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ክብር ፡ ምልክት ፡ ቆጥሮት ፡ ለምን ፡ ቀረብኝ ፡ ብሎ ፡ እንደኢያ ፡ ከጉደታ ፡ ጋር ፡ እንደተጣሉት፡

ሰውዬ ፡ ያለቅሳል ። ጉደታ ፡ ይልቅ ፡ ጎበዝ ፡ ነው ። እማርኛው ፡ ይጥፋው ፡ እንጂ ፡ የግብር ፡ መሰረት ፡ ምን ፡ መሆኑን ፡ የሚ ያውቅ ይመስላል ።” አለ ። ከዚያ ፡ ጉደታ ፡ ኢንጉሲን ፡ ጊብሪ ፡ ጊዲዳት ፡ በላልናንጂ ፡ ውድዳት ፡ በላልና ?” ያለው ፡ ትዝ ፡ አለ ውና ፡ ብቻውን ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ።

እንጋት ፡ ላይ ፡ ትንሽ ፡ እንቅልፍ ፡ ሊወስደው ፡ ሲል ፡ ነጋዴ ዎች ፡ ሲንጫጩ ፡ ተነሳ ። ከዚያ ፡ ቡና ፡ ጠጥቶ ፡ ወደ ፡ ደብተራ ፡ መንበሩ ፡ ሄደ ።

“አንተ ፡ እድላም ፡ ነህ ፡ እባክህ !” አለ ፡ ደብተራ ፡ መን በሩ ፡ በፃብህን ፡ ከሩቁ ፡ ሲያይ ፡ እንዴት ፡ አደርህ ፡ ከማለቱ ፡ እንኮዋ ፡ አስቀድሞ ።

“ እንዴት ? ” አለ ፡ በፃብህ ፡ ልቡ ፡ በደስታ ፡ ፈንጥዞ ፡ ካፎቱ ፡ ሊወጣ ፡ እንደ ፡ ፊለገ ፡ ሁሉ ፡ በደረቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲንደ ፋደፍ ፡ ክሩቅ ፡ እዬተሰማ ።

“እድላም ፡ ነህ ፡ የቅኔ ፡ ችሎታህን ፡ እንደ ፡ ነገርኸኝ ፡ አደ፡ርጌ ፡ ትንሽም ፡ ሠዓማምሬ ፡ ሰነግራትው ፡ ዘጣም ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ “ ደህና ፡ ነው ፡ ስራውን ፡ ይጀምር ፡ ” አሉ ። “ ብቻ - - - - - ረስቸ - - - - - - - ትናንት ፡ ያልነገርሁህ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ። ”

“ምን ?”

“ ቦታው ፡ ከፍተኛ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መሸዋማያ ፡ ይከፈልበታል፡

“ ምን ፡ ያክል ? ”

“ መቶ ፡ ብር ። ”

“ መቶ ፡ ብር፟ማ ፡ የት ፡ አገኛለሁ ? ”

“ መቶ ፡ ብር ፡ ከሌሎች ፡ የሚቀበሉት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግ / ፡ አንተን ፡ አጥብቀው ፡ የሚፈልጉህ ፡ ስለሚመስሉ ፡ መቶም ፡ ባይሞላ ፡ ይቀበሉ ፡ ይሠሩል ፡ እንዲያው ፡ ግን ፡ እንደማይ ሰጡህ ፡ እር፡ግጠኛ ፡ ነኝ ። ”

ነጋዴ፡ራስ ፡ ሠነኛው ፡ ይሆን ፡ ሲሰሙ ፡ አንድ ፡ ጅምብ ፡ ግርና ፡ አንድ ፡ ጅምብ ፡ ቅቤ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ለደብተራ ፡

መንበሩ ፡ ታል ፡ ሰሱ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ በዛብህ ፡ ከራሱ ፡ ሀያ ፡ ብር ፡ ጨምሮ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነቱን ፡ አገኘ ። ከዚያ ፡ ንጋድራስ ፡ ሁኖው ፡ ወዳገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ስራ ፡ መያዙንና ፡ የሚኖርበ ትን ፡ ቦታ ፡ ዘርዝሮ ፡ ጽፎ ፡ እግረ ፡ መንገዳቸውን ፡ ሲያልፉ ፡ ዲግ ፡ ለጉዱ ፡ ካሣ ፡ ሰጥተውለት ፡ እንዲያልፉ ፡ አደራ ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።

ምእራፍ ፡ ፴

መርዶ ፡

ሰው ፡ ደስታ ፡ የሚያገኘው ፡ ሀብት ፡ በማግኘት ፡ ለነገ ፡ ሹመትና ፡ ሽልማት ፡ በመታጨት ፡ ዜናው ፡ ተሰፋፍቶ ፡ በመ ለማት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በዛብህ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በደረሰ ፡ ባሞር ፡ ገዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ አገኘ ።

የያዘው ፡ ስራ ፡ ባገልግሎት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከቆ ዩት ፡ እንኩዋ ፡ ጥቂት ፡ እድላሞች ፡ ብቻ ፡ ሊደርሱበት ፡ የሚ ችሉ ፡ እሱም ፡ አገኝዋለሁ ፡ ብሎ ፡ በሞራሽ ፡ ተስፋ ፡ ያላደረ ገው ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ስራ ፡ ነው ። ባመት ፡ መቶ ፡ ብርና ፡ በወር ፡ ሶስት ፡ ዳውላ ፡ እህል ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሰም ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ማደሪያ ፡ እንኩዋንስ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ በወጡ ፡ ግማስት ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ አገልግሎት ፡ በሁዋላም ፡ ቢሆን ፡ ብድር ፡ ይከፍላል ፡ የሚባል ፡ ወገንና ፡ ጉበ ፡ የሚሰጡት ፡ ብዙ ፡ ሀብት ፡ የሌላቸው ፡ የሚያገኙት ፡ አይደለም ። ስሙም ፡ እንደ ፡ የሩሳሌም ፡ ባላዩት ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀና ፡ የግኑን ፡ ሆነ ።

“ ከስመጥሩ ፡ ካለቃ ፡ ከንፉ ፡ ተመርቆ ፡ የወጣ ፡ ሊቅ ፡ የሩፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ወንበር ፡ ያዘ ፡ ” ተብሎ ፡ እን ደተወራ ፡ መልኩን ፡ ያላዩት ፡ ቅኔውን ፡ ያልሰሙት ፡ ያዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አሰቆች ፡ ሁሉ ፡ እንዱ ፡ ደመወዙን ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ሁለት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ ላድርግ ፡ ሲል ፡ እን ዲሁ ፡ እንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ እሰጣለሁ ፡ በማለት ፡ አባብለው ፡ ወደዱደብራቸው ፡ ለመውሰድ ፡ ይጫ ረቱበት ፡ ጀመር ። ያዲስ ፡ አበባ ፡ ካህናት ፡ በዱመሀራው ፡ የሚያወሩት ፡ አዲሱ ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ያለቃ ፡ ከንፉ ፡ ደቀ መዝሙር ፡ መሆኑንና ፡ የሩፋኤልን ፡ ወሬ ፡ ነበር ። ሩፋኤል ፡ እንኩዋ ፡ በበዛብህ ፡ ምክናያት ፡ ለጊዜው ፡ ስመጥር ፡ ሆነ ፡

ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የተሰበሰበው ፡ ተማሪ ፡ ቁጥሩ ፡ ይዘን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ እያ ባልም ። የዘፃብዘን ፡ ቤት ፡ ከዕ ፡ የተሰራው ፡ የተማሪ ፡ ጎጇ ፡ ሚዳውን ፡ የዘግች ፡ ሰፈር ፡ አስመስለው ። ያውም ፡ ከዬቤት ፡ ተመላልሶ ፡ ከሚማረው ፡ ሊላ ፡ ነው ። ጊዜ ፡ ባለፈ ፡ መጠን ፡ እዬተቀነሰ ፡ ሄደ ፡ እንጂ ፡ እመጀመሪያው ፡ ላይማ ፡ ከተማሪ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ሚዳው ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ የሰፈሩም ፡ ሰው ፡ መመረር ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

መቸም ፡ እንኩዋንስ ፡ እንደ ፡ በዘፃብዘ ፡ ያለቃ ፡ ከንፋን ፡ ትልቅ ፡ ሰም ፡ ያስከተለ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ አዲስ ፡ አስተማሪ ፡ አዲስ ፡ እንደ ፡ ፈለቀ ፡ ጠበል ፡ ዜናው ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ግናና ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዬጠበሉ ፡ ሥረው ፡ ተስፋ ፡ የቆረጡ ፡ እውሮችና ፡ ደንቆሮዎች ፡ ወደም ፡ ሌላ ፡ በሽተኞች ፡ አዲስ ፡ ጠበል ፡ ፈለቀ ፡ ሲሉዋቸው ፡ ባዲስ ፡ ተስፋ ፡ ወዳ ዲሱ ፡ ጠበል ፡ እንደሚሽቀዳደሙ ፡ እንዲሁም ፡ የቅኔ ፡ ምስ ጢር ፡ ሰለ ፡ ተሰወራችው ፡ የዘማ ፡ ጣም ፡ ስላልተሰማቸው ፡ ከትምርት ፡ የሸሸ ፡ ትምርት ፡ አልገባቸው ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ደዲስ ፡ አስተማሪ ፡ ወሬ ፡ ሲሰሙ ፡ ደነገ ፡ አእምሮዋቸውን ፡ እውጥቶ ፡ ጥሎ ፡ አዲስ ፡ ስለት ፡ አእምሮ ፡ እንደሚተካላቸው ፡ ወደሱ ፡ መጉረፋቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። እንደነሱ ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ እን ሄዳለን ፡ ብሎ ፡ ማውራት ፡ ከብር ፡ የሚመስላቸው ፡ ዲያቆ ናት ፡ ተፈሕረው ፡ ቅኔ ፡ ቤቱን ፡ የሜዳ ፡ ገብያ ፡ አስመሰ ሉት ። በሁዋላ ፡ ብቻ ፡ ለመብራት ፡ በተስፋ ፡ የመጡት ፡ የቅኔ ፡ እውሮችና ፡ ለወሬ ፡ የመጡት ፡ ዲያቆናት ፡ ትንሽ ፡ በትንሽ ፡ ወደዬመጡበት ፡ ተመልሰው ፡ በውነት ፡ ቅኔ ፡ ለመ ማር ፡ ፈቅዱም ፡ ችሎታውም ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ የሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የቅኔ ፡ ቤት ፡ መልክ ፡ አገኘ ። ያም ፡ ሆኖ ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ በሩፋኤል ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ተማሪ ፡ ሩብ ፡ እንኩዋ ፡ ያሉው ፡ እንድም ፡ አልነበረ ።

አለቃ ፡ ስርግው ፡ የሩፋኤሉ ፡ አለቃ ፡ በበኩላቸው ፡

ደዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ በዘፃብዘን ፡ እንደ ፡ ከፋ ፡ ቀን ፡ እህል ፡ ሲሻሙት ፡ እደከፍሉ ፡ ከፍለው ፡ ለመውሰድ ፡ ሲፈልጉ ፡ ሲያዩ ፡ ሁሉንም ፡ እሸንፈው ፡ ከሳቸው ፡ ጋር ፡ ሊያስቀሩት ፡ የሚችሉበትን ፡ ዘዴ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ። በደ መወዝ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ያክል ፡ ጭማሬ ፡ በሌያደርጉ ፡ የጊ ዮርጊስና ፡ የሌሎች ፡ ዘበታም ፡ አድባራት ፡ አለቆች ፡ ከሚ ሰጡት ፡ ጋር ፡ ለመወዳደር ፡ እንደማይችሉ ፡ ያውቃሉ ። ስለ ዚህ ፡ በደመወዝ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ማግኘት ፡ አለባቸው ። ጸአዳ ፡ ስርግው ፡ ያለጥርጥር ፡ ደዲስ ፡ አበባ ፡ አድባራት ፡ ሁሉ ፡ እንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ሊሰጡ ፡ ከሚችሉት ፡ ደመወዝ ፡ ትበልጣለች ! ጸአዳ ፡ ለአለቃ ፡ ስር ግው ፡ ተቀዳሚ ፡ ተከታይ ፡ የሌላት ፡ እንዲት ፡ ልጃቸው ፡ ናት ። ባል ፡ ባገባች ፡ በሶስት ፡ ሳምንትዋ ፡ ተፋታ ፡ ተመልሳ ፡ አባትዋም ፡ እንደ ፡ ፈታችው ፡ ባልዋ ፡ ከምሽት ፡ ጋር ፡ መር ፡ የሞላ ፡ አብረው ፡ መቆዬት ፡ ስለማይችሉ ፡ እንድዋ ፡ ምሽት ፡ ሄዳ ፡ ሌላዋ ፡ እስክትመጣ ፡ እሽክሮቻቸውን ፡ እሰማረች ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ቤታቸውን ፡ አስተዳዳሪ ፡ አሰዋ ፡ ናት ። እንደ ፡ ምሽት ፡ መለወጫ ፡ የሌላት ፡ አለችኝ ፡ ብለው ፡ የሚኮሩባት ፡ አስካሉ ፡ የምኞት ፡ ይሁን ፡ የችግር ፡ ተካፋያቸው ፡ ሲያልፉ ፡ ወረሻቸው ፡ ናት ። እስዋን ፡ ከዳሩሰት ፡ የጸአዳ ፡ ባል ፡ ያለቃ ፡ ስርግው ፡ የልጅ ፡ ባል ፡ ከሆነ ፡ በዘፃብዘ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ይዘን ፡ የሚያስለውጥ ፡ ዋጋ ፡ አገኘለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደማያ ስብ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ሩፋኤል ፡ የቅኔ ፡ መም ህራን ፡ ሁሉ ፡ ካዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ ከየት ፡ እዬተሰበሰበ ፡ የሚመረቁበት ፡ ስመጥር ፡ ይሆናል ! ሰው ፡ ሁሉ ፡ “ እድሚ ፡ ላለቃ ፡ ስርግው ፡ ሩፋኤልን ፡ ከወደቀበት ፡ እንስተው ፡ የሊ ቃውንቱ ፡ የቅኔ ፡ መመሳከሪያ ፡ አደረጉት ! ከሁሉ ፡ በታች ፡ የነበረውን ፡ ከሁሉ ፡ በላይ ፡ እደረጉት ነ” ይላል ። ከዚያ ፡ በሁ ዋላ ፡ ይህ ፡ ድንቅ ፡ ስራቸው ፡ ለከፍተኛ ፡ ሹመት ፡ ባያሳጫ ቸው ፡ ሩፋኤልን ፡ እሻራለሁ ፡ ብለው ፡ እንዳይሰጉ ፡ የታመነ ፡ ዋስ ፡ ይሆናል ! ከዚያ ፡ ልጃቸውን ፡ ላንድ ፡ ስም ፡ የሌለው ፡ የቅኔ ፡ መምህር ፡ ሰጡ ፡ እንዳይባሉ ፡ የበዛብሀን ፡ ሙያና ፡

የልጃቸው ፡ ባል ፡ መሆኑን ፡ ለጃንሆይ ፡ ነግረው ፡ በቅኔ ፡ መም ህርነቱ ፡ ላይ ፡ ሽመትና ፡ ሽልማት ፡ ሲያሰጡት ፡ የሳቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሱም ፡ የልጃቸውም ፡ ጥቅም ፡ ያሐበቀል ! ጎድቶ ፡ መጠቀም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠቅሞ ፡ መጠቀም ፡ በሰ ውም ፡ ሆነ ፡ በእግዚአብሄር ፡ ዘንድ ፡ አያስወቅስም ! አዎ ! እን ዲህ ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የግዜር ፡ ስጦታ ፡ የሚ ያስለውጥ ፡ ከጊዮርጊስም ፡ ይሁን ፡ ከሌላ ፡ ደብር ፡ ሊያገኝ ፡ አይ ችልም ። ይህ ፡ ነው ፡ ማሸነፈያቸው ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አሰባቸው ።

እውነትስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የግዚአብሄር ፡ ስጦታ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ድንገት ፡ ሳይታሰብ ፡ እንዲሁ ፡ ከጥሩ ፡ ሰማያ ፡ ሲዘንብለት ፡ ደስ ፡ የማይለው ፡ ማነው ? ልቡ ፡ ካፎቱ ፡ ወጥቶ ፡ በደስታ ፡ ክንፍ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የማያርግ ፡ የማይሰርግ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ? - - - - - - - - - የምኞትን ፡ የደስታን ፡ የስልጣንንና ፡ እነሱን ፡ የመሰሉትን ፡ የሰው ፡ ፍላጎቶች ፡ ይዞ ተፈጥሮ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ እድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ ደስ ፡ የማይ ለው ፡ ሰው ፡ እያገኘም !

በቫብህ ፡ ራሱ ፡ እንዲያ ፡ በቅኔ ፡ ገብያ ፡ ብቻውን ፡ ተገ ኝቶ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚጫረትበት ፡ መሆኑን ፡ ሳያረጋ ፡ የሩፋ ኤልን ፡ ተራ ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ በማግኘቱ ፡ እንኮዋ ፡ የነ በረው ፡ ደስታ ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ያስቸገራል ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ የመጣው ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ በላም ፡ የራቀ ፡ ስለነበረ ፡ እደርስበት ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አስቦትም ፡ ተመኝቶ ትም ፡ የማያውቅ ፡ ነገር ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በልሙ ፡ ወይም ፡ ሰብለን ፡ የሚ ያኖርበት ፡ በደጌ ፡ ፍሰጋ ፡ ራሱን ፡ ሲበጠብጥ ፡- ያንድ ፡ ደብር ፡ አለቅኔት ፡ ወይም ፡ ሊቀጠበብትነት ፡ ይሾምና ፡ ሀር ፡ ሲለብስ ፡ ባለድግድግ ፡ መረሻት ፡ በቅሎ ፡ ሲያስጭን ፡ እቤቱ ፡ ስጋ ፡ እንደ ፡ ጎመንና ፡ ዱባ ፡ ሲቆረጥ ፡ ጠጅና ፡ አረቂ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ሲፈስ ፡ በነፍተኛ ፡ ፍራሽና ፡ ለሰላሳ ፡ ሀር ፡ ምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ጎን ፡ ለጎን ፡ ተቀምጦ ፡ ከግራቀኝ ፡ መከዳዎች ፡ መጠበል ፡ ሲንፈላሰስ ፡ ይቆይና ፡ ድንገት ፡ ከንቅልፉ ፡ ሲነቃ ፡

ወይም ፡ አእምሮውን ፡ ሲገዛ ፡- ያ ፡ ሁሉ ፡ ውሸት ፡ ያ ፡ ሁሉ ፡ ጨዋታ ፡ መሆኑን ፡ ሲያይ ፡ ሲቀልድበት ፡ ቆይቶ ፡ በሄደው ፡ እልም ፡ ወይም ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ብቻውን ፡ ይስቃል ። ይህ ፡ መቸም ፡ እልም ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አእምሮ ፡ ሲታወክ ፡ የሚመጣ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ ነው ። አእምሮውን ፡ ገዝቶ ፡ ቁሜ ፡ ብሎ ፡ ስለኑሮው ፡ ሲያስብ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አገኛ ለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ይቅርና ፡ ምኞት ፡ እንኮዋ ፡ አልነበረውም ።

ጣ ስራ ፡ ሳልይዝ ፡ ሰብለ ፡ ትደርስና ፡ ትችገርብኛለች ፡ ብሎ ፡ ሲፈራና ፡ ሲሸበር ፡ ለሰው ፡ ፍቅር ፡ የታደለ ፡ በመሆኑ ፡ ንጋድ ራስ ፡ ሁኔኛው ፡ ከመንገዳቸው ፡ ወጥተው ፡ ረድተውት ፡ የሩ ፋኤልን ፡ የቅኔ ፡ መምህርነት ፡ ሲያገኝ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለው ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ፈጣውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ቤት ፡ ሰፈ ፡ ሚዳ ፡ የከበበው ፡ ቤት ፡ ካቅሙ ፡ በላይ ፡ ተከራይቶ ፡ በውስጥ ፡ ግር ግዳውንና ፡ ወለሉን ፡ ባመድ ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ አስለቅልቆ ፡ ሰብለ ፡ እውሜ ፡ ተቀምጣ ፡ ሚዳውን ፡ የምትመለከትበት ፡ ባርሜግና ፡ ሌላም ፡ እወዳለሁ ፡ ስትል ፡ ከሰማው ፡ እቃ ፡ የሚች ለውን ፡ ያክል ፡ ገዝቶ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አሽ ከር ፡ ቀጥሮ ፡ ሰብለን ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ ይዞ ፡ ይደርሳል ፡ እ ያለ ፡ በናፍቆት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ። ቤተ ፡ ክርስተያን ፡ አገልግሎ ቱንና ፡ ቅኔ ፡ ቤት ፡ ማስተማሩን ፡ ሲጨርስ ፡ ግረፍ ፡ ወይም ፡ መ ሜወት ፡ ሳያምረው ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ ይሰፍርበታል ፡ በሚባለው መደብር ፡ ሁሉ ፡ እዩዞረ ፡ ከዲግ ፡ ወይም ፡ ከሞጣና ፡ ከቢችና ፡ የመጣ ፡ ነጋዴ ፡ ሲፈልግ ፡ ራስዋን ፡ ተሸፍና ፡ በበቅሎ ፡ ተቀ ምጣ ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ ወንዶች ፡ ያጀብዋት ፡ ወይዘሮ ፡ ባዬ ፡ ቀ. ጥር ፡ እንደ ፡ ሰላይ ፡ ያላዩ ፡ መስሎ ፡ ለማየት ፡ ሲከተል ፡ ሁለት ፡ ሶስት ፡ አራት ፡ ወር ፡ አለፈ ። እንኮዋን ፡ ሰብለን ፡ ወሬዋን ፡ የሚ ያመጣ ፡ ሰው ፡ ጠፋ ። ነጋድራስ ፡ ሁነኛው ፡ እንኮዋን ፡ ደህና ፡ ከሆነው ፡ ገናን ፡ ተመልሼ ፡ እቤቴ ፡ ለመዋል ፡ እንድችል ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ እመጣለሁ ፡ ያሉት ፡ ሳይመጡ ፡ ቀሩ ፡ የሚያደርገውን ፡ እጣ ። ግራ ፡ ገባው ። ማነን ፡ ይጥራ ? የማን ፡ ያለህ ፡ ይበል ?

እንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሽምብራ ፡ ብቻ ፡ ቆርጥሞ ፡ ውሀ ፡ እዪጠጣ ፡ ሶስትም ፡ ሰባትም ፡ ቀን ፡ እዪጸመ ፡ ሲጸልይ ፡ እንኩዋ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ አልም ፡ አያይም ። የሚያየውም ፡ ያክል ፡ የሚያስፈራራ ትዝ ፡ እንጂ ፡ የሚያጽናና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ጊዜ ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ ሰብለን ፡ የግግኘቱ ፡ ተስፋ ፡ እዪተቀነሰ ፡ እያነሰ ፡ መሄድ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ያ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡ እያለ ፡ አብሮት ፡ የሚኖረው ፡ በሄደበት ፡ ሁሉ ፡ የሚከ ተለው ፡ ፍራት ፡ ባሳቡ ፡ ውስጥ ፡ እዪጎላ ፡ ይታዪው ፡ ጀመር ። ገና ፡ ሲፈጠር ፡ ፈጣሪው ፡ የመደበለትን ፡ ህይወት ፡ በመሸሹ ፡ ወላጆቹንም ፡ እግዚአብሄርንም ፡ የበደለ ፡ መሆኑ ፡ ቅጣት ፡ የሚጎሳው ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑ ፡ በጉልህ ፡ ድምጽ ፡ ራሱ ፡ ውስጥ ፡ ሲጮህ ፡ ይሰማው ጀመር ። ለመሰዋትነት ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ኖሮ ፡ ለግለፍ ፡ ያልተፈጠረ ፡ መሆኑን ፡ ይጠረ ጥር ፡ ጀመር ።

“ብቻ ፡ ለምን ? ከተወለድሁ ፡ ጀምሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ሊያስፈርድብኝ ፡ የሚችል ፡ በደል ፡ እግዚአብሄርን ፡ አልበደልሁም ! ሳልወለድም ፡ ልበድለው ፡ አልችልም ! ታዲያ ፡ ሳልበድል ፡ ለምን ፡ የግዞት ፡ ኑሮ ፡ እንድኖር ፡ ይፈረድ ብኛል ? ” ይላል ፡ በዛብህ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ እግዚአብሄር ፡ ባልበደሉት ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የሚፈር ድበት ፡ ምክናያት ፡ አልገባው ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ለሚ ፡ ያለ ፡ ዳኛ ፡ እዪተሙዋገተ ።

ከዚህ ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ከደረሰው ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በጠቅላላው ፡ ሰው ፡ የሚኖርበት ፡ የግሀበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ስራት ፡ ይታዪዋል ። በጌታኖ ፡ በባሪያ ፡ በስጋዊም ፡ ሆነ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ገዢዎችኖ ፡ በተገዢው ፡ ህዝብ ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ በግፍ ፡ ባድልዎና ፡ በጭካኔ ፡ ላይ ፡ የተመሰረተ ፡ ስራት ፡ ይታዪዋል ። ከዚያ ፡ ደካማ ፡ ይደገፍበታል ፡ የተበደለ ፡ ይካሰበታል ፡ የሰው ፡ መብትኖ ፡ ነጻነት ፡ ይከበርበታል ፡ ብሎ ፡ ይገምተው ፡ የነበረው ፡ የንጉሱ ፡ አደባባይ ፡ ደካማ ፡ በመጀገፍ ፡ ፈንታ ፡ ወድቆ ፡ የሚገጥበት ፡ የተበደለ ፡ ሰው ፡ እንኩዋንስ ፡ ሊካስ ፡ ተበደልሁ ፡ ብሎ ፡ ለማኩረፍ ፡ ነጻነት ፡ የማያገኝበት ፡ መሆኑን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እግ

ብር ፡ ላይ ፡ ያዪው ፡ ትዝ ፡ ይለዋል ። ከዚያ ፡ የመንፈሳዊ ፡ መሪ ዎችኖ ፡ አስተማሪዎች ፡ ነን ፡ በሚሉት ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ስጋውያን ፡ ገዢዎች ፡ ከሚያደርጉት ፡ የማያንስ ፡ መገበያየት ፡ ጉቦ ፡ ግፍ ፡ በደል ፡ ተንኮል ፡ ሁሉ ፡ ይታዪዋል ።

“ እም ፡ አለሙ ፡ እንደ ፡ ለማኝ ፡ እህል ፡ ድብልቅልቅ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ባለጌዎች ፡ ሸንጎ ፡ ትልቅ ፡ ድምጽ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ እንዲሰሙበት ፡ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ያላቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲያሸንፉ በት ፡ ሆኖ ፡ የተሰራ ፡ ነው ! እኔም ፡ ተሰሚ ፡ ድምጽኖ ፡ ብርቱ ፡ ጡንቻ ፡ ከሌላቸው ፡ እንዱ ፡ ነኝ ! ብቻ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እንዲሆን ፡ ያደረገው ፡ ግኑው ? እግዚአብሄር ፡ ነው ? ወይሰ ፡ ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደሚለው ፡ ልግድ ፡ ነው ? ” ይላል ፡ በዛብህ ፡ የግያዩ ፡ አይናቹን ፡ ፍጥኖ ፡ አድርጎ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተከሉ ። “ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይንኖ ፡ ጆሮ ፡ በሌለው ፡ አድልም ፡ ላይ ፡ የተ መሰረተ ፡ ሰራት ፡ እውነት ፡ አዋቂው ፡ ትክክለኛው ፡ ቸሩ ፡ ትልቁ ፡ እግዚአብሄር ፡ የሰራው ፡ ነው ? እሱስ ፡ ባይሰራው ፡ የሰሩትንኖ ፡ ሲሰሩት ፡ የሚኖሩትን ፡ ለምን ፡ ዝም ፡ ይላቸዋል ? እንጂ ! የሱ ፡ ስራት ፡ አይደለም ፡ እንዳልል ፡ ጌታኖ ፡ ባርያ ፡ ገዢ ፡ ንጉስኖ ፡ ተገዢ ፡ ህዝብ ፡ አባትኖ ፡ እናት ፡ ልጃቸውን ፡ እንደ ፡ ያእቀብ ፡ መሰዋእት ፡ አድርገው ፡ ማቅረብ ፡ ሁሉ ፡ ከአሪት ፡ ጀምሮ ፡ በመ ጽሀፍ ፡ ይገኛል ! እሱ ፡ የሰራው ፡ ስራት ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ ፍጥ ረቱን ፡ ያላንዳች ፡ ምክናያት ፡ በበዳይኖ ፡ በተበዳይ ፡ መሀከል ፡ እንዲከፋፈል ፡ ግድረግ ፡ ያልበደለ ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቀጣ ፡ የበደለ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ በደለ ፡ እንዲኖር ፡ ግድረግ ፡ እን ኩዋንስ ፡ ያዋቆች ፡ ሁሉ ፡ አዋቂ ፡ የሆነው ፡ እግዚአብሄር ፡ የመ ንደር ፡ ዳኛም ፡ የሚፈርደው ፡ አይደለ ! ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ነው ? እንጂ ! ”

በዛብህ ፡ እንዲህ ፡ ሊኖር ፡ ወይሰ ፡ ላይኖር ፡ የተፈጠረ ፡ መሆ ኑን ፡ ግወቅ ፡ አቅቶት ፡ ይህ ፡ አለም ፡ ተጠይፈው ፡ ጥለውት ፡ ሊሄዱ ፡ ወይሰ ፡ በውስጡ ፡ ተቀምጦ ፡ ግፍ ፡ ሊቀበሉበት ፡ ወይም ፡ ከግፍ ፡ ሰሪዎች ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ግፍ ፡ ሊሰሩበት ፡ የሚገባ ፡ መሆ ኑን ፡ ግወቅ ፡ አቅቶት ፡ ሲጨነቅ ፡ “ የጊዮርጊስ ፡ አለቃ ፡ ደመ ወዝህን ፡ እጥፍ ፡ አደርግልህለሁኖ ፡ ሞጥተህ ፡ እንነጋገር ፡ አሉህ ፡

የመድሀኔ ፡ አለም ፡ አለቃ ፡ ሶስት ፡ እጥፍ ፡ አደርግልሀለሁ፡ ብለው ሀል ፤ የስላሴ ፡ አለቃ ፡ ከጃንሆይ ፡ ጋር ፡ አገናኝሀለሁ ፡ ብለው ሀል ፡ አለቃ፡ስርግው ፡ አደራህ ፡ በሞቴ ፡ አፈር ፡ ስሆን ፡ ዛሬ ፡ ሰራት ፡ እንዳትቀር ፡ እጠብቅሀለሁ ፡ ብለውሀል ።። "የሚል ፡ መላ ክተኛ ፡ ከዬወገኑ ፡ ይላክበትና ፡ እነሱ ፡ ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ የሚጠ ይቁትን ፡ ለመቀበልም ፤ ላለመቀበልም ፡ በሚችልበት ፡ ሁኔታ ፡ ስላልሆነ ፡ ከሁሉም ፡ መሸሸን ፡ ይፈልጋል ።። ነገር ፡ ግን፡ ከሁሉም፡ ቢያመልጥ ፡ ካለቃ ፡ ስርግው ፡ ማምለጡ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ።።

አለቃ ፡ ስርገው ፡ በዛብህን ፡ በልጃቸው ፡ ለመማረክ ፡ ሰለ ወሰኑ ፡ ልማድ ፡ አድርገው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ከራት ፡ በሁዋላ ፡ ከልጃ ቸው ፡ ጋር ፡ ትተውት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክናያት ፡ እዬፈጠሩ ፡ ሲወጡ ፡ ብቻውን ፡ ክጸአዳ ፡ ጋር ፡ የሚቆይበት ፡ጊዜ ፡ ከተወለደ፡ ጀምሮ ፡ ከኖረው ፡ አድሜ ፡ ረዝሞ ፡ ይታዬዋል ።።

ጸአዳ ፡ ቁንጅናዋን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚያደንቀው ፡ ቀጠን ፡ ረዘም ፡ ያለች ፡ ፊትዋ ፡ ሰልከክ ፡ አይናችዋ ፡ ጎላ ፡ ያሉ ፡ አፍን ጫዋ ፡ ከላይ ፡ ቀጭ ፡ ከመሀከል ፡ ሰጉደድ ፡ ያለ ፡ ከንፈሮችዋ ፡ አነስ ፡ አነስ ፡ ብለው ፡ የሸፈኑዋቸውን ፡ ያልማዝ ፡ ድርድር ፡ የመ ሰሉ ፡ ጥቃቅን ፡ ጥርሶችዋን ፡ ገለጥ ፡ ሲያደርጉ ፡ ደስ ፡ የምትልና ፡ ልቅም ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ ያላት ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ናት ።። ለበዛብህ ፡ ግን ፡ ህይወትና ፡ ሙቀት ፡ የሌለው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ፈዛዛ ፡ ገና ፡ ቀለም ፡ ያልተቀባ ፡ የስእል ፡ ንድፍ ፡ እንጂ ፡ አጥንትና ፡ ስጋ ፡ ደምና ፡ ቆዳ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ መስላ ፡ አትታዬውም ፡ ነበር ።። ጸአዳ ፡ ሴቱን ፡ ሁሉ ፡ ካስጠሉት ፡ አንድዋ ፡ ናት ።።

አንድ ፡ ቀን ፡ አባትዋ ፡ እንደ ፡ ነገሩዋት ፡ እጠገቡ ፡ ተቀምጣ፡ እያጫወቱች ፡ ጠጅ ፡ ቀድታ ፡ ስትሰጠው ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ ተነካ ኩና ፡ ልክ ፡ በረዶ ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ቅዝቃዜዋ ፡ የሰራ ፡ አካላቱን ፡ ያደነዘዘው ፡ መሰለው ።። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ መጥላት ፡ ብቻ ፡ ሳይ ሆን ፡ እንደ ፡ ጣረሞት ፡ ይፈራት ፡ ጀመረ ።። እሰዋም ፡ ብትሆን ፡ አብራው ፡ በተቀመጠች ፡ ቁጥር ፡ ሲጨነቅና ፡ መድረሻ ፡ ሲያጣ፡ እያዬች ፡ እንደሚጠላት ፡ ተረድታ ፡ ያባትዋን ፡ ፈቃድና ፡ ትእ ዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ግዴታ ፡ ሆናባት ፡ አብራው ፡ ተቀምጣ ፡ መ

ጠጥ ፡ ስትጋብዘው ፡ ትቆያለች ፡ እንጂ ፡ የራስዋ ፡ ፈቃድ ፡ ቢኖራት ፡ ጠልቶዋት ፡ ያን ፡ ያክል ፡ ሲቸገር ፡ ማየት ፡ ልክ ፡ የሞት ፡ ያክል ፡ የምትጠላው ፡ ነገር ፡ ነው ።።

ከጸአዳ ፡ ቀጥላ ፡ በዛብህን ፡ ለማጥመድ ፡ የሞከረች ፡ ተዋ በች ፡ ናት ።። ተዋበች ፡ ቤትዋ ፡ በዛብህ ፡ በሚወጣ ፡ በሚገባበት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይተያያሉ ።። ከመተያየትና ፡ ሰላምታ ፡ ከመለዋወጥ ፡ ያለፈ ፡ እውቂያ ፡ ግን ፡ አልነበራቸውም ።። በቁጥር ፡ መልክም ፡ ሆነ ፡ በደም ፡ ግባት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የሚያደ ንቃትና ፡ ብዙ ፡ መኩዋንንት ፡ የሚጣሉባት ፡ በመሆንዋ ፡ በዛ ብህ ፡ እንዲሁ ፡ ሰላምታ ፡ ብቻ ፡ እዬሰጣት ፡ ማለፉና ፡ በውበ ትዋ ፡ አለመማረኩ ፡ አስቆጭቶዋት ፡ ኩርፊያውንም ፡ ግልምጫ ውንም ፡ ሌላውንም ፡ ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ አሳብ ፡ ወደነሱ ፡ የሚ ስቡበትን ፡ ዘዴ ፡ ሁሉ ፡ ሞክራ ፡ ሲያቅታት ፡ ጊዜ ፡ የሴቶችን ፡ ትታ ፡ የወንዶችን ፡ መንገድ ፡ ለመከተል ፡ ወሰነች ።። አንድ ፡ ቀን፡ በዛብህ ፡ አራዳ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ ፍለጋ ፡ ሄዶ ፡ ቆይቶ ፡ ሲመ ለስ ፡ ተዋበች ፡ እቤትዋ ፡ ጥግ ፡ ተቀምጣ ፡ ጠብቃ ፡ " እንዴት ፡ አመሸህ ፡ አለቃ ፡" አለችው ።። "እግዚአብሄር ፡ ይመስገን ፡ ማነው ?" አለ ፡ በዛብህ ፡ መሸቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ተዋበች ፡ መሆን ዋን ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ስላልቻለ ።።

"እኔ ፡ ነኝ ፡" አለች ፡ ተዋበች ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ተነስታ ፡ ወደሱ ፡ እዬሄደች ።። "ወንድሜ ፡ ካገር ፡ ቤት ፡ ወረቀት ፡ ልኮልኝ ፡ የሚያነብልኝ ፡ አጣሁ ፡ እባክህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እቤት ፡ ግባና ፡ አንብብልኝ ።።"

"የማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ደርሶብኛል ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ ባለኝ ፡ ነበር።።"

"መጻፍስ ፡ አይደለም ፤ ማንበብ ፡ ነው ።። ማንበብ ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳል?"

እቤት ፡ ሲገቡ ፡ ተዋበች ፡ ከጉዋዳ ፡ በወረቀት ፡ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ ብርሌ ፡ ጠጅ ፡ አምጥታ ፡ አንዱን ፡ ለሱ ፡ ሰጠችና ፡ አንዱን ፡ እሰዋ ፡ ይዛ ፡ አጠገቡ ፡ ተቀመጠች ።።

"ወረቀቱ ፡ የታል?" ላንብብልሽና ፡ ልሂድ ፡ እባክሽ ።።"

"ፈጥኖ ፡ ከመሄድ ፡ ያድንህ ፡ ይላል ፡ መራቂ ! ፈጥኖ ፡ መሄድ ፡ ደግ ፡ አይደለም !"

እዬተቀነሰ ፡ ሄደ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰራውን ፡ ጨርሶ ፡ ቁጭ ፡ ሲል ፡ ወይም ፡ ሌሊት ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ቃልኪዳን ፡ ከተገባላቸው ፡ ታቦቶችና ፡ ከወላጆቹ ፡ በመሸፈቱ ፡ እግዚአብሄር ፡ የተጣላው ፡ በደለኛ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ይለውና ፡ ፍራት ፡ ሲይዘው ፡ በጸሎት ፡ ከእግዚአብሄር ፡ ለመታረቅ ፡ ሁሉንም ፡ ጥሎ ፡ መመ ነን ፡ ያስባል ።

"ሽፍታ ፡ ቀማኛ ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ አመንዝራ ፡ ልሆን ፡ አል ሸሸሁ ! በሀጥ ፡ እግብኜ ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ይዤ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ እያገለገልሁ ፡ ለመኖር ፡ ብሸሽ ፡ ምን ፡ ጥፋት ፡ አደረ ግሁ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሄር ፡ ይቆጣኛል? የለም! በዚህ ፡ የሚቆጣ ፡ አይመስለኝም! ብቻ ፡ እኔ ፡ መበደል ፡ አለመበደሌን ፡ እሱ ፡ መቆ ጣት ፡ አለመቆጣቱን ፡ እንዴት ፡ ግወቅ ፡ ይቻላል?" ይላል ፡ እን ደገና ፡ መልሶ ።

አንድ ፡ ሌሊት ፡ ይህኑ ፡ ሲያሰላስል ፡ ድምጽ ፡ የሰማ መሰ ለውና ፡ በጣም ፡ ደንግጦ ፡ አይኑንም ፡ አፉንም ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ በሰፈው ፡ ከፍቶ ፡ አሳቡን ፡ ጥቅልል ፡ አድርጎ ፡ ያዳ ምጥ ፡ ጀመረ ። የሰማው ፡ ድምጽ ፡ አእምሮው ፡ በአሳብ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ ሳይታወቀው ፡ ከፊሱ ፡ ይውጣ ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ በጭሯሽ ፡ ሊረዳው ፡ አልቻለም ።

"ይህ ፡ እኮ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያክል ፡ አያስቸ ግርም ። ሰብለ ፡ እስከ ፡ ፋሲካ ፡ ካልመጣች ፡ እግዚአብሄር ፡ ያል ፈቀደ ፡ መሆኑን ፡ ተረድቶ ፡ ነገሱን ፡ እግዚአብሄር ፡ የመይበ ውን ፡ መንገድ ፡ መከተል ፡ ነው ።" ፡ የ ሚል ፡ ነበር ፡ ድምጹ ።

"ጥሩ ፡ መልስ ፡ ነው !" አለ ፡ በዛብህ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ሲያ ዳምጥ ፡ ቆይቶ ። "እንግዲህ ፡ አምላኬ ፡ እስከ ፡ ፋሲካ ፡ ከሰብለ ፡ ጋር ፡ ያገናኘኸኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለሌላው ፡ ፍጥረትህ ፡ ሁሉ ፡ የፈቀ ድኸውን ፡ ሀይወት ፡ ለኔ ፡ ያልነፈግኸኝ ፡ መሆንህንና ፡ እስከዛ ሬም ፡ የነበረኝ ፡ ፍራት ፡ ከንቱ ፡ መሆኑን ፡ እረዳለሁ!ካልመጣች፡ ግን ፡ ያው - - - - የምጠረጥረውና ፡ የምፈራው ፡ እውነት ፡ መሆኑ፡ ነው!"

"እቤቴስ ፡ ነው ፡ ወደሌላ ፡ ልሂድ ፡ አላልሁም! "

"ምሽት ፡ የሌለው ፡ ወንድ ፡ ሴት ፡ ያለችበት ፡ ሁሉ፡ቤቱ ፡ ነው!" አለችና ፡ እንገቱን ፡ በሁለት ፡ እጆዋ ፡ ጥምጥም ፡ አድ ርጋ ፡ ይዛ ፡ ለመከላከል ፡ ብርሌውን ፡ እስኪያስቀምጥ ፡ ድረስ ፡ አፉን ፡ ባፍዋ ፡ ጎርሳ ፡ ላመችው ። በዛብህ ፡ ብርሌውን ፡ አስቀ ምጦ ፡ ልስ ፡ ከጣሪሞት ፡ ለማምለጥ ፡ እንደሚጣጣር ፡ ሀይሉን ፡ ሁሉ ፡ አጠራቀመና ፡ ከላዩ ፡ ገፍትሮ ፡ ጥሎዋት ፡ ተነሳ ፡ ፍራት፡ ከቁጣ ፡ ጋር ፡ ተጨምሮ ፡ እያንቀጠቀጠው ። ተዋበች ፡ በበኩልዋ፡ ከወደቀችበት ፡ ለመነሳት ፡ ስትጣጣር ፡ ዘቅዝቆ ፡ ቢመሰከታት፡ ጠጉርዋ ፡ ጭብርር ፡ ፊትዋ ፡ ከርሮ ፡ አይንዋም ፡ አፍዋም ፡ በሰ ፊው ፡ ክፍት ፡ ብሎ ፡ እውነትም ፡ ጣረሞት ፡ መስላ ፡ ታዬችው። ከዚያ ፡ አፉን ፡ እዬጠረገ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሮጠ ።

ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ በተዋበች ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ማለፉን ፡ እንኩዋ ፡ እዬፈራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይሁን ፡ ወደ ፡ ሌላ፡ የሚሄድበትን ፡ መንገድ ፡ ሰወጠ ። ስለዚህ ፡ በጸአዳና ፡ በተዋ በች ፡ ምክናያት ፡ ሴቱን ፡ ሁሉ ፡ መጥላት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ይፈራ፡ ጀመር ። በጸአዳና ፡ በተዋበች ፡ ምክናያት ፡ ከሰብለ ፡ በቀር ፡ ሌላው ፡ ሴት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተዋበች ፡ የሚባላ ፡ እንደ ፡ ጸአዳ ፡ ቅዝቃዜው ፡ የሚያደነዝዝ ፡ መስሎ ፡ ታዬው ። በተዋበችና ፡ በጸ አዳ ፡ ምክናያት ፡ እግዚያብሄር ፡ በለፊ ፡ መሬቱ ፡ ከሰብለ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ ያልፈጠረ ፡ መስሎ ፡ ታዬው ። ሰብለን ፡ ካላገኘ፡ሌላ፡ ምሽት ፡ አግብቶ ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ መኖር ፡ የማይችል፡መስሎ፡ ታዬው ። አገሩን ፡ ለቆ ፡ የተሰደደበት ፡ ወላጆቹ ፡ እንደ ፡ መካ ኖች ፡ ያላስታማሚ ፡ በባዶ ፡ ቤት ፡ ታመው ፡ እንዲሞቱ ፡ ያደረ ገበት ፡ ዋና ፡ አላማው ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱ ፡ ታዬው ።

በዛብህ ፡ ገና ፡ ድሮ ፡ አገሩ ፡ ማንኩላ ፡ ዲያቆን ፡ ሆኖ ፡ ሲቀ ድስ ፡ ጀምሮ ፡ ከሁሉ ፡ አብልጦ ፡ የሚመኛቸው ፡ ሁለት ፡ ነገ ሮች ፡ ነበሩ ። የመጀመሪያው ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ምሽት ፡ አግ ብቶ ፡ ንብረት ፡ አበጅቶ ፡ መኖር ፡ ሁለተኛው ፡ በተሰይ ፡ የቅኔ ፡ ሊቅ ፡ መሆን ፡ ናቸው ። ሀብታም ፡ መሆን ፡ ሰብለን ፡ ከወደደ ፡ በሁዋላ ፡ የጨመረው ፡ ሶስተኛ ፡ ምኞት ፡ ነው ። የሰብለ ፡ ወሬ ፡ እዬራቀው ፡ ሲሄድ ፡ እንኩዋ ፡ የሀብት ፡ የመኖር ፡ ምኞቱም ፡

በልማዱ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ የገናንም ፡ ይሁን ፡ የፋሲካን ፡ አመትባል ፡ ተመልሶ ፡ በዱቤቱ ፡ ለመዋል ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ካመትባሉ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የንግድ ፡ እቃውን ፡ እዬጫነ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መድረስ ፡ አለበት ።። በዛብህ ፡ ይህን ፡ ስላጠና ፡ የገና ፡ አመትባል ፡ እስኪያልፍ ፡ ያደርገው ፡ እንደነበረ ፡ ሁሉ ፡ ከፋሲካ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ያክል ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴ ፡ የሚሰፍርበትን ፡ መደብር ፡ ሁሉ ፡ በቀን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይረግጠው ፡ ውሎ ፡ አያድርም ።።

አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ በዬመደብሩ ፡ ሲዘር ፡ አምሽቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲመለስ ፡ ሁለት ፡ የጎጃም ፡ ነጋዴዎች ፡ እዬተጫወቱ ፡ ወደ ፡ ጉለሌ ፡ ሲሄዱ ፡ ደረሰባቸው ።።

“ አሁንስ ፡ አሲ ፡ ጀብሪ ፡ ቆዳችንን ፡ መዝንልንና ፡ ዋጋ ፡ እንነጋገር ፡ ብንለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሚዛኑ ፡ ተሰብሮዋል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መዛኙ ፡ ታሙዋል ፡ እያለ ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ የሚሰን ፡ ፋሲካ ፡ እስኪደርስለት ፡ ነው ! ” አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ።።

“ፋሲካ ፡ ሚዛን ፡ ይሆናል ? ወይስ ፡ መዛኝ ! ” አለ ፡ ሁለተኛው ።።

“የለም ፡ ዛሬ ፡ ነገ ፡ እያልሁ ፡ ፋሲካ ፡ እስኪሰግት ፡ ካቆዬሁዋቸው ፡ ለማጫረት ፡ ጊዜ ፡ ያጥራቸውና ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ ጥለውልኝ ፡ ይሄዳሉ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ! ”

“አረግ ፡ የዲማው ፡ አባቴ ! ዋጋ ፡ ስብረን ፡ ከምንሸጥ ፡ በምናውቀው ፡ አገር ፡ አስቀምጠነው ፡ እንሄድም ?”

“ ላዲስ ፡ አበባ ፡ እንግዶች ፡ መስለነው ፡ ይሆናል።”

ነጋዴው ፡ የዲማን ፡ ስም ፡ ሲጠራ ፡ በዛብህ ፡ ልቡ ፡ ተር ተር ፡ ብሎ ፡ በህዋሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ወራሪ ፡ ተነዝቶ ፡ የሚበዘብዘው ፡ መስሎ ፡ ተሰማው ።። ጉልበቱ ፡ እንደ ፡ መብረክረክ ፡ አይኖቹ ፡ ትንሽ ፡ እንደ ፡ መድበዝበዝ ፡ አሉና ፡ ወዲያው ፡ የተናወጸ ፡ አካላቱ ፡ ጸጥ ፡ አሳቡም ፡ ጠቅሰል ፡ አለ ።። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ነጋዴዎች ፡ የተነጋገሩትን ፡ አልሰማም።።

“ጌቶች ፡ ከየት ፡ ጎጃም ፡ ነው ፡ የመጣችሁ? እኔ ፡ ጎጃሜ ፡ ስለሆንሁ ፡ ያገሬ ፡ ለምች ፡ መሆናችሁን ፡ ስለተረዳሁ ፡ ነው ፡

ደፍሬ ፡ የምጠይቃችሁ ።” አለ ፡ አስተካከሉ ፡ ለመናገር ፡ እስኪችል ፡ ትንሽ ፡ ቆይቶ ።

“ ከነማይ ። ” አለ ፡ አንዱ ፡ ነጋዴ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በዛብህን ፡ አዬና ።

“ የት ፡ እነማይ ? ”

“ ዲማ ። ”

“ ዲማ ፡ ይብሩ ? ”

“ ዲማ ፡ እምብዙ። ”

“ ዲማ ፡ ማነን ፡ ታውቃላችሁ ? ፈታውራሪ ----- መሸሻን ፡ ታውቃላችሁ ?”

“እሮ ! ምን ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ አያ ! ዲማ ፡ እዬኖርን ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ያጥፉን ? ”

“አለቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤንሳ ?”

“እዋ! ጉዱ ፡ ካሳን ?”

“ ታዲያ ፡ ሁሉም ፡ ይህና ፡ ናቸው ? ”

“ ይህና ፡ ናቸው ። ”

“ አለቃ ፡ ካሳ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልኝ ፡ ስጠብቃቸው ፡ ስለቀሩ ፡ ይህና ፡ ባይሆኑ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ሰግቼ ፡ ነበር ።”

“ ሁሉም ፡ ደህና ፡ ናቸው ፡ ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡ ይሰናዳሉ ። ሰርጌም ፡ ታስካሬም ፡ የልጂ ፡ ሰርግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስታውቀው ፡ እነማይ ፡ በሙሉ ፡ ይደግሳል ። እኛ ፡ እንኩዋ ፡ ከዚህ ፡ ለሙሽራዋም ፡ ለሙሽራውም ፡ የሚሰጡት ፡ ሽልማት ፡ ገዝተን ፡ እንድንወስድላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተውን ፡ ነበር ፤ አይነቱን ፡ የሚመርጥልን ፡ አጥተን ፡ ገና ፡ አልገዛንም ። ጌታው ፡ እንግዲህ ፡ እስዎ ፡ ዘመድ ፡ ከሆኑ ፡ ለትልቅ ፡ ሰው ፡ ሽልማት ፡ የሚሆን ፡ ልብስ ፡ መምረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ቢያጋጥሙን !” አለና ፡ ነጋዴው ፡ መልስ ፡ ሲያጣ ፡ ጊዜ ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ በዛብህ ፡ በሁዋላቸው ፡ የለም ።

በዛብህ ፡ ነጋዴው ፡ “ፈታውራሪ ፡ መሸሻ ፡ ልጃቸውን ፡ ለፋሲካ ፡ ሊድሩ ፡” ሲል ፡ መብረቅ ፡ እንደመታው ፡ በቆመበት ፡ ደርቆ ፡ ቀረ ። ወዲያው ፡ ሳይታወቀው ፡ እዚያው ፡ ተቀመጠ ። ከዚያ ፡ በሁዋላ ፡ ነጋዴው ፡ የተናገረው ፡ ሁሉ ፡ ከጉዋደኛው ፡

በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰሚ ፡ አልነበረውም ። ሁለቱ ፡ ነጋዴዎች ፡ በዛ ብሀን ፡ በሩቅ ፡ ተቀምጠ ፡ ሲያዩት ፡ ታምዋል ፡ ብለው ፡ ወደሱ ፡ እዩርጡ ፡ ሄዱ ። ለጊዜው ፡ መነሳት ፡ ያቅተው ፡ እንጂ ፡ አእምሮውን ፡ ገዝቶ ፡ እገኙት ።

“ ምነው ? አመመዎ ? ” አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡

“ ትንሽ ፡ ራሴን ፡ አዙሮኝ ፡ ነው ፡ ግዴለም ፡ ሂዱ ፡ አዙን ፡ ይተውኛል ። ”

“ መጠኖ ፡ ጠጥተው ፡ ሞርሞል ! ”

“ የለም ፡ መንሾ ፡ አለብኝ ፡ አዙን ፡ ግን ፡ ማለፉ ፡ ነውና ፡ አትቸኩሩ ፡ ሂዱ ። ”

“ እንደ ፡ ደመኛ ፡ አመንነድ ፡ ላይ ፡ ጥለንዎ ፡ እንሂዳለን ? ስለራችን ፡ እዚህ ፡ ነው ፡ ዙኖ ፡ ጠጥተው ፡ ሲሻለዎ ፡ እቤትዎ ፡ እናድርስዎ ፡ እንጂ ! ”

በዛብህ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ነጋዴዎች ፡ ወደ ፡ ተከራዩት ፡ ቤት ፡ አብሮዋቸው ፡ ሄዶ ፡ ዙኖ ፡ ሲጠጡ ፡-

“ ወደ ፡ ዲማ ፡ መቸ ፡ ለመነሳት ፡ ታስባላችሁ ? ” አለ ።

“ ከዛሬ ፡ ሳምንት ፡ እናልፍም ። ”

“ እስክትሄዱ ፡ ድረስ ፡ እዩመጣሁ ፡ እጠያቸዋለሁ ።”

ከዚያንለት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ ይሁን ፡ እረፍት ፡ የለው ፡ የመብል ፡ ይሁን ፡ የመጠጥ ፡ ፍላጎት ፡ የለው ፡ ገና ፡ መብል ፡ ሲያስብ ፡ አፉን ፡ እዩመረረው ፡ ራሱ ፡ እስበላቸው ፡ የሚጣሉ ፡ አሳቦች ፡ የሚዋጉበት ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሆኖ ፡ ደከመው ።

“እዚያው ፡ ዲግ ፡ ብቆይ ፡ ኖሮ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ አይደርስም ፡ ነበር ! ምን ፡ ለማድረግ ፡ እችል ፡ ኖርዋል ? ጉዱ ፡ ካሳ ፡ ወዳጄ ፡ መስሎ ፡ አታሎ ፡ ሰዶ ፡ ጉድ ፡ አደረገኝ ! አይ ፡ የለም ፡ ባይሆንለት ፡ ነው ! ሰብለ ፡ ካያችኝ ፡ የለም ፡ ተግዳ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ፈቅዳ ፡ አይደለም ! በግድ ፡ ነው ! በቃችኝ ፡ ጠላሁዋት ፡ እንግዲህ ፡ አባትዋ ፡ በግድ ፡ አንቀው ፡ ሲሸጥዋት ፡ ምን ፡ አደረግሽ ፡ ብዬ ፡ ልጥላት?”

በዛብህ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ያሳብ ፡ ውሽንፍር ፡ ሲያጠናፍረው ፡ ሰንብቶ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የታወከ ፡ የአሳብ ፡ ማእበል ፡

ሶስት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ሲያንገላታው ፡ ሰንብቶ ፡ በመጨረሻ ፡ ያለ ጥፋት ፡ ከተፈረደበት ፡ ቅጣት ፡ ለማምለጥ ፡ ከሙታን ፡ ኑሮ ፡ የህያዋን ፡ ኑሮ ፡ ለመኖር ፡ ከጀመረው ፡ ትግል ፡ ድል ፡ መሆኑን ፡ አምኖ ፡ መሸነፉን ፡ ተቀብሎ ፡ ጸጥ ፡ ማለት ፡ ማረፍ ፡ ጀመረ ። ተንጠልጥሎ ፡ እወድቅ ፡ አልወድቅ ፡ ከማለት ፡ መውደቅ ፡ በሰንት ፡ ጣሙ! መውደቅ ፡ ያሳርፋል! ስለዚህ ፡ በዛብህ ፡ ወደቀኖ ፡ አረፈ ። አንድ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ዲማ ፡ ነጋዴዎች ፡ ቤት ፡ ቢሄድ ፡ ወዳገራቸው ፡ ለመነሳት ፡ ሞኑታቸውን ፡ ሲቀረቃቅቡ ፡ ደረሰባቸው ።

“እኛስ ፡ ሲቀሩ ፡ ጊዜ ፡ ሳናገኝዎ ፡ ልንሄድ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ፈርተን ፡ ነበር ።” አለ ፡ ከነጋዴዎቹ ፡ አንዱ ፡ በዛብህን ፡ ሲያይ ፡

“ጤና ፡ አጥቼ ፡ ሰነበትሁ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ላሊቃ ፡ ካሳ ፡ ዳምጤ ፡ ታያርሱልኛላችሁ?” አለ ፡ በዛብህ ፡ አንድ ፡ አንሼሎን ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ።

“የገባሁ ፡ እለት ፡ እሰጣቸዋለሁ ፡ እቤቱም ፡ አላሳድረው ፡” አለ ፡ ነጋዴው ፡ እዬሳቀ ።

“ይድረሳቸው ፡ እንጂ ፡ ቢያሳድሩትም ፡ ግዴለ ።”

ነጋዴው ፡ እንዳለው ፡ ዲማ ፡ የገባለት ፡ ደብዳቤውን ፡ ለጉዱ ፡ ካሳ ፡ አስረከበ ። የተጻፈው ፡ ለስብለ ፡ ለስ ፡ ነበረ ፡ በዘነጋው ፡ ደረሳት ፡ በዛብህና ፡ እሰዋ ፡ ላጭር ፡ ጊዜ ፡ የፍቅር ፡ አለማቸውን ፡ ባዩባት ፡ እልፍኝዋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጣ ፡ አነበበችው ።የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ ነው!

“ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ሰብለ ፡ ወዳጄ ፡ እመቤቴ ፡-
የመአልት ፡ ምርኮዬ ፡ የሌሊት ፡ መብራቴ ፡-
ስሪብ ፡ እንጀራዬ ፡ ስሸማ ፡ ወተቴ ፡-
ሳዝን ፡ መጽናኛየ ፡ ሰያከነም ፡ ጉልበቴ ፡-
ሳጣ ፡ አለኝታየ ፡ ስሰቃ ፡ ከራቴ ፡-
የስጋ ፡ የመንፈስ ፡ ያለሽኝ ፡ አንድ ፡ ብቴ ፡-
ቁርጥ ፡ ከሆነማ ፡ እኔ ፡ አንቺን ፡ ማጣቴ ፡-
ምን ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ ከንግዲህ ፡ ዘይወቴ?
የለም! ዘይወት ፡ በቃኝ! ይገላግለኝ ፡ ሞቴ ፡-
ተቀማሁ ፡ ውዴኔ ፡ ድህ ፡ በመሆኔ ፡-

ጥቁሽ ፡ የሄደሁለት ፡ ወንዝ ፡ ተሻግሬ ፡-
የደም ፡ እንባ ፡ አልቅሼ ፡ በድሌ ፡ እግርሬ ፡-
የሁዋሊት ፡ ስዕተት ፡ በፍቅርሽ ፡ ታስሬ ፡-
ወደፊት ፡ መራመድ ፡ እያቃተው ፡ እግሬ ፡-
አሁንም ፡ አሁንም ፡ ቆሜ ፡ እያዩሁ ፡ ዞሬ ፡-
ምን ፡ ልቤ ፡ ቢፈራ ፡ ባይቀር ፡ መጠርጠሬ ፡-
በተስፋ ፡ ነበረ ፡ የመጣሁ ፡ ካገሬ ፡-
እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ በህይወት ፡ መኖሬ ፡-
ተስፋ ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ፡ ፍቅርሽና ፡ ፍቅሬ ፡-
ግን ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ የነገሩኝ ፡ ወሬ ፡-
ሊያገባሽ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባለብዙ ፡ በቅሎ ፡ ባለብዙ፡ በሬ፡-
በፍቅር ፡ ለሞተ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆኖ ፡ እንዲኖር ፡ መቃብሬ ፡-
መናር ፡ አልፈልግም ፡ ሞቼ ፡ ልያር ፡ ዛሬ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድህ ፡ በመሆኔ ፡
ለብለ ፡ ልጠይቅሽ ፡ እስቲ ፡ ተናገሪ ፡
ከሁሉ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ እንደምታፈቅሪ ፡-
ከኔ ፡ ተለይተሽ ፡ እንዳትችይ ፡ ልትኖሪ ፡-
ላባትሽ ፡ ነግረሻል ፡ በድፍረት ፡ ሳትፈሪ ፡-
እንቢኝ ፡ አሻፈረኝ ፡ ያለሽ ፡ አላገባም ፡ ብለሻል ፡ ሳታፍሪ ?
ወይስ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ታፍኖ ፡ ተዳሪ ፡-
ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተቀበልሽ ፡ ሳትከራከሪ?
ወይስ ፡ ተለይተን ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስትኖሪ ፡-
መቸም ፡ ሰው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ሲፈጥረው ፡ ፈጣሪ ፡-
ተለውጦ ፡ ይሆን ፡ ከቶ ፡ ያንችም ፡ ባህሪ ፡-
የለም ፡ ማሪኝ! ማሪኝ! ርሺ ፡ አትዘከሪ ፡-
ዱብዳ ፡ ወድቆብኝ ፡ ለሽከሙ ፡ አስቸጋሪ ፡-
ጨንቆኝ ፡ ስለፈልፍ ፡ እንደ ፡ ቀባጣሪ ፡-
ባንቺ ፡ እምነት ፡ የሌለኝ ፡ ብመስል ፡ ጠርጣሪ ፡-
መሆንሽን ፡ አውቃለሁ ፡ ፍቅሮሽን ፡ አክባሪ ፡-
በሀብት ፡ ለመደለል ፡ የማትሞክሪ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድህ ፡ በመሆኔ ፡
አውቃለሁ ፡ አባትሽን ፡ እንዳማጠንሻቸው ፡-

ነፍስና ፡ ስጋ ፡ ነን ፡ እባክዎ ፡ አይለዩን ፡ አባባ! እንዳልሻቸው፡
ከዚህ ፡ አይሻለሁ ፡ ወድቀሽ ፡ ከፈታቸው ፡-
እዬተሰቀዩሽ ፡ ስትለምኛቸው ፡-
እንባሽ ፡ ይታዩኛል ፡ ሲፈስ ፡ በግራቸው ፡-
አየ! ያባት ፡ ክፉ ፡ ምቀን ፡ የሞላቸው ፡-
እስቲ ፡ እኛ ፡ ደስ ፡ ቢለን ፡ ምኑ ፡ ጎድሉባቸው ፡-
የሳቸውን ፡ ህይወት ፡ ኖረው ፡ በፈንታቸው ፡-
የኛን ፡ ህይወት ፡ እንዲህ ፡ ከንቱ ፡ ማድረጋቸው ?
እኔስ ፡ ባእዳቸው ፡ ነኝ ፡ ይቅር ፡ ልበላቸው !
ደስታ ፡ በብዙ ፡ ሀብት ፡ ይገዛ ፡ መስሎዋቸው ፡-
እንዴት ፡ ይነግዱ ፡ በገዛ ፡ ልጃቸው ?
ዳኛ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ የሚጠይቃቸው ፡-
ከቶ ፡ የሚሰጡት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ መልሳቸው ?
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !..
ዳኛ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ቢኖርማ ፡ ዳኛ ፡-
ሀሊናው ፡ ባድልዎ ፡ በጉቦ ፡ ያልተኛ ፡-
እንዳንቺ ፡ አባት ፡ ያለ ፡ ጨካኝ ፡ አመጸኛ ፡
በልጁ ፡ የሚነግድ ፡ ሲገኝ ፡ ግፈኛ ፡-
እጁን ፡ ወደሁዋሊት ፡ ታስሮ ፡ በመጫኛ ፡-
ይሰቀል ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
እግዚአ ፡ አቤት ፡ አቤት ፡ ለማን ፡ ልጨህ ፡ እኔ ?
ነፍሴን ፡ መስደውብኝ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ በድኔ ፡
አልቅሶ ፡ እንዳይቀብረኝ ፡ እንዳያዝን ፡ ወገኔ ፡-
ቆሞ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ይታየል ፡ ግብኔ ፡-
በማን ፡ ያረሶ ፡ ያውቃል ፡ እንዲህ ያል ፡ ብያኔ ?
ሳያጠፉ ፡ ቅጣት ፡ ሳይሞቱ ፡ ኩነኔ ?
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግዴለም !
ጉልበቴን ፡ ሳላጥፍ ፡ መገቢን ሳልፈታ ፡-
ቀን እረፍት ፡ ሳያምረኝ ፡ ወደ ፡ ሌሊት ፡ ምኝታ ፡-
እርም ፡ ብዬ ፡ ትቸ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ጭዋታ ፡-
ስጸልይ ፡ ስማለል ፡ ከጥዋት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡-

ያሳዩኛል ፡ ብዬ ፡ አይንሽን ፡ ላንድ ፡ አፍታ ፡-
አጥፊዎችን ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ ባዩ ፡ ጌታ ፡-
መቸም ፡ ያልጻፈኝ ፡ ነኝ ፡ ስፈጠር ፡ ላደስታ ፡-
አመጣልኝ ፡ መርዶ ፡ በምስራች ፡ ፈንታ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግደለም !
እግዚአብሄር ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ጥንቱን ፡ በዚህ ፡ መራት፡-
ሳለቅስ ፡ ተወልጄ ፡ ሳለቅስ ፡ ኖሬበት ፡-
ሳለቅስ ፡ እንድሄድ ፡ ነው ፡ ወደማልቀርበት ?
መሀረ ፡ ጠግቤ ፡ ይስታ ፡ እንድራብበት ?
ሌሎች ፡ የበሉትን ፡ እዳ ፡ እንድከፍልበት ?
ሌላው ፡ ጠግቦ ፡ ሲያደር ፡ እኔ ፡ እንዳልቀምስበት ፡
እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ፍርድ ፡ አድሎ ፡ የሞላበት ፡-
አቅም ፡ ስለሌለኝ ፡ የምቀመምበት ፡-
ገም ፡ ብዬ ፡ እቀሰልሁ ፡ መቸስ ፡ ምናለበት ፡
ብቻ ፡ ሳላጠፋ ፡ በተቀጣሁበት ፡-
የሰጠኝ ፡ አእምሮ ፡ ልመረመርበት ፡-
ቅንና ፡ ጠማማ ፡ ለይቼ ፡ እንዳውቅበት ፡
ምንም ፡ እንኩዋ ፡ ባይችል ፡ ቅጣት ፡ ሊጥልበት ፡
ይኖራል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ፈረደበት ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግደለም !
እኔኮ ፡ ግደለም ፡ ይቅጣኝ ፡ ይደብድበኝ ፡-
መቸም ፡ ለመከራ ፡ ለጣር ፡ የመደበኝ ፡-
ሳዘን ፡ ኖሬ ፡ እንድሞት ፡ የተፈጠርሁ ፡ ነኝ ፡-
አንጀቴን ፡ የበላው ፡ አሁን ፡ ያሳዘነኝ ፡-
ታምሜ ፡ እማልድነው ፡ በሽታ ፡ የሆነኝ ፡-
እሱ ፡ የጠላኝን ፡ ተጣኝተሽ ፡ ስትወጂ ፡-
አንቺንም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ መቅጣቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡-
ዳሩ ፡ ዳኛ ፡ የለም ! ልተወው ፡ ግደለም !
ከልብ ፡ የሚያስማማ ፡ በመድ ፡ ወዳጅ ፡ ጠፍቶ ፡-
ጨነቀኝ ፡ ጠበበኝ ፡ ምን ፡ ላርግ ፡ ይሆን ፡ ከቶ !
እንጀራ ፡ በመሶብ ፡ ጠጅ ፡ በንስራ ፡ ሞልቶ ፡-
ቴትነት ፡ ሊጠራኝ ፡ በሩን ፡ በዋ ፡ አሉን ፡ ከፍቶ ፡-

ሹመት ፡ ሲለምነኝ ፡ እጀቹን ፡ ዘርግቶ ፡-
ልቤ ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ ሰብለ ፡ ላንቺ ፡ አድልቶ ፡-
ጌትነት ፡ ያላንቺ ፡ ከንቱነቱን ፡ አይቶ ፡-
አንች ፡ በሌለሽበት ፡ መደስትን ፡ ጠልቶ ፡-
ወዳጁን ፡ ከሀዲ ፡ እንዳይባል ፡ ፈርቶ ፡-
ሁሉንም ፡ አንቢ ፡ አለ ፡ ድምጹን ፡ አሰምቶ ፡-
ምከረው ፡ እባክሽ ፡ አርፎ ፡ እንዲያሳርፈኝ ፡ ከንቱ ፡ ትግሉን
ትቶ ።
ድል ፡ ከሆኑ ፡ በላይ ፡ መዘረፍ ፡ የማይቀር ፡ መሆኑን ፡ ተረ
ድቶ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ልቤን ፡ ባባብለው ፡ ተጽናናልኝ ፡ ብዬ ፡-
እንቢ ፡ አለኝ ፡ ምን ፡ ላርገው ፡ ንገሪኝ ፡ ሰብልዬ ፡-
ካንቺ ፡ ከሚወድሽ ፡ ስለተለየዬ ፡-
ቀን ፡ ከሌት ፡ ያለቅሳል ፡ ይላል ፡ ወዬ ፡ ወዬ ፡
በጦር ፡ እንደመቱት ፡ እዬ ፡ ተሰቀዬ ፡
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ሰብለ ፡ የኔ ፡ ተስፋ ፡ የልቤ ፡ ደስታ ፡
የመንፈሴ ፡ ድጋፍ ፡ ያሳበ ፡ ጸጥታ ፡
መቸም ፡ ልንገናኝ ፡ አልፈቀደም ፡ ጌታ ፡
ብናለቅስ ፡ አ ፡ ብንል ፡ ደረት ፡ ብንመታ ፡-
አንግዴህ ፡ እንተወው ፡ ይከተተው ፡ ዝምታ ፡-
ብቻ ፡ እንዳትረሺ ፡ የፍቅሬን ፡ ትዝታ ፡-
ቀን ፡ ስትቀመጪ ፡ ስትተኚ ፡ ማታ ፡-
እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኚ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አይለይሽ ፡ የማዚአብ
ሄር ፡ ርዳታ ፡-
መከፋት ፡ አይንካሽ ፡ የልብ ፡ ቅሬታ ፡
ካለሽበት ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ሳለሽበት ፡ ቦታ ፡-
ተቀማሁ ፡ ወይኔ ፡ ድሀ ፡ በመሆኔ !
ለባለድል ፡ ከሆንሽ ፡ እኔ ፡ ስላልታደልሁ ፡-
በደስታ ፡ እንድትኖሪ ፡ እመኝልሻለሁ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ ከንግዴህ ፡ ካንቺ ፡ ከተለዬሁ ፡-

ልቤን ፡ ለሌላ ፡ ሴት ፡ እንዳልሰጥ ፡ ምያሰው ፡-
እስኪጠራኝ ፡ ድረስ ፡ በሀያወት ፡ እስካለው ፡-
ከትዝታሽ ፡ ጋራ ፡ ቆርቤ ፡ እኖራለው ።
እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሁኝ ፣ ባያሌው ፡ ደህና ፡ ሁኝ ፡ ሰላም ፡ ብዬሻለሁ !
ወይኔ ፡ ወይኔ ፡ ተቀግሁ ፡ ወይኔ ፡ ድህ ፡ በመሆኔ !”
“ በፅ፟ብህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልግሎቱን ፡ የተወበት ፡ ምክናያት ፡ ምንድ፟ነው ? ደብተራ ፡ መንበሩ !” አሉ ፡ አለቃ ፡ ስርግው ፡ አንድ ፡ ቀን ።
“ ከቤት ፡ ከጠፉ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ስለሆነ ፡ ተግሪው ፡ ሁሉ ፡ መበተን ፡ መጀመሩን ፡ አልሰሙም ? ጌታየ ! ”

ምእራፍ ፡ ፴፩ ፡

ሰርግ፟ና ፡ ተዝካር ፡

በፅ፟ብህ ፡ ዲማን ፡ ትቶ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ከሄደ ፡ በሁዋላ ፡ ወዲያው ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ፈታውራሪ ፡ ታፈረ ፡ ድንበሩ ፡ ሰብለን ፡ አጭተው ፡ ሰርጉ ፡ ለገ፟ና ፡ እንዲሆን ፡ ተወሰነ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመሀከሉ ፡ ሰብለ ፡ በጽኑ ፡ ታማ ፡ የገ፟ና፟ን ፡ አመትባል ፡ ሁሉ ፡ ትተርፍ ፡ አትተርፍ ፡ እዬተባለ ፡ ቤተ፟ዘመዱ ፡ ገና ፡ በስጋት ፡ ላይ ፡ ስለነበረ ፡ ለገ፟ና ፡ የተቀጠረው ፡ ሰርግ ፡ ወደ ፡ ሩሲካ ፡ ተላለፈ ።

ቀኑ ፡ ሲደርስ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ በዙወገኑ ፡ በዝርዝር ፡ ሲሰናዳ ፡ የኖረው ፡ ድግስን ፡ ድግስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እዬሆነ ፡ የመጨረሻ ፡ መልኩን ፡ መያዝ ፡ ጀመረ ። ዳሱ ፡ መሰራት ፡ እንጀራው ፡ መጋገር ፡ ጠጁ፟ና ፡ ጠላው ፡ በዙጋኑ ፡ መሞ፟ም ፡ ወጡ ፡ በያይነቱ ፡ መሰራት ፡ ጀመረ ።

እቤት ፡ ከሚሰናዳው ፡ ሌላ ፡ እንደያትግቸው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ ፍሪዳ ፡ እያረዱ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ በላይ ፡ አቆልቱዋይ ፡ የሚይዙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያስታወቁ ፡ የፈታውራሪ ፡ መሸሻ፟ና ፡ የወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ አይነት ፡ ባለቁርጥ ፡ ዘመዶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በዚያ ፡ ላይ ፡ ከነግይ ፡ ካወባ ልና ፡ ከጥላትግን ፡ ከጎንቻ፟ና ፡ ከሳር ፡ ምድር ፡ ለደስታው ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተጠሩ ፡ መኩዋንንትና፟ ፡ ስማቸው ፡ የታወቀ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እንደያትግቸው ፡ ፍሪዳ ፡ በግ ፡ ግር ፡ ወይም ፡ ቅቤ ፡ ያልሰጡ ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ። ፈታውራሪ ፡ የራሳቸው ፡ ሀብት ፡ አልበቃቸው ፡ ብሉ ፡ ከዲግ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እዬተ ወደሩ ፡ የገ፟ቱ፟ና ፡ ከዙመኩዋንንቱ ፡ የተላከላቸው ፡ ፍሪዳና፟ ፡ በግ ፡ በዙጋጋው ፡ ታግዶ ፡ ሲታይ ፡ ብዛቱ ፡ የነግይን ፡ የጎንቻ፟ና ፡ የሳር ፡ ምድርን ፡ ያወባልንና ፡ የጥላትግንን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡